# ምዕራፍ ፬

# ጋሼ ሳህሌ ጃፎ

ሐምሌ 18 ቀን 2004 ዓ.ም በከምባታ ጠምባሮ ዞን በምትገኘው አንጋጫ ወረዳ ውስጥ ታላቅ በዓል የሚከበር ይመስል በርካቶች በወረዳው ውስጥ ወደምትገኘው የዲንቃ ቀበሌ ተምመዋል። በወቅቱ ከአዲስ አበባ የሄዱ የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን መሪዎችና ሌሎችም፤ የሐዲያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን መሪዎች፣ አገልጋዮችና ምእመናን፤ የከምባታ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን መሪዎች አገልጋዮችና ምእመናን ሌሎችም ከልዩ ልዩ ስፍራዎች የመጡ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እና አገልጋዮች በስፍራው ተገኝተዋል። ይኽ ሁሉ ሕዝብ በስፍራው የመገኘቱ ምክንያትም በዚሁ አካባቢ ተወልደው በከምባታ፣ በሃዲያ በጌዴኦና በሌሎች ስፍራዎች ተዘዋውረው ወንጌል የሰበኩትን ታላቅ የወንጌል አርበኛ አባት ሳህሌ ጃፎን የቀብር ሥነ ሥርዓት ለመታደም ነበር።

በወቅቱ እኚህ አንጋፋ የወንጌል አርበኛ አባት ያገለገሉት ጌታ እንዲኖሩ የፈቀደላቸውን እድሜ ጠግበው በ88 ዓመታቸው ሐምሌ 15 ቀን 2004 ዓ.ም በሞት መለየታቸው በየአካባቢው ተነግሮ በርካቶች በሦስተኛው ቀን ይካሄዳል የተባለው ቀብር ላይ ተገኝተዋል።

ምንም እንኳን ወርኃ ሐምሌ በአካባቢው ከባድ ዝናብ የሚጥልበትና በጊዜው የሚታየው ደመናና የሰማዩ ጉምጉምታ ዝናቡ ሊዘንብ እያስፈራራ የነበረበት ቢሆንም፤ በስፍራው የተገኘው ሕዝብ ከስድስት አስርት ዓመታት በላይ ወንጌልን ያገለገሉትን እኚህን ጎምቱ የወንጌል አርበኛ ለመሰናበት ቆርጦ የቀብር ስነ ሥርዓቱ ላይ ተገኝቷል።

በዚህ ወቅት በስፍራው ተገኝተው ለቀብር ስነ ሥርዓቱ ታዳሚ መልዕክት ያቀረቡት ወንጌላዊ ኬዳሞ ሜቻቶ ነበሩ። ወንጌላዊው በዚህ ቀብር ላይ መልዕክት አቅራቢ ሆነው የተገኙት የቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን አንጋፋ አገልጋይ እና በበርካታ መሰል ሥነ ስርዓቶች ላይ ተናጋሪ ሆነው በተደጋጋሚ ይቀርቡ ስለነበር ብቻ አልነበረም። ይልቁንም በዕለቱ ቀብራቸው የሚካሄደው ወንጌላዊ ሳህሌ የወንጌላዊ ኬዳሞ የቅርብ መንፈሳዊ አባት ስለሆኑም ጭምር ነበር።

*ወንጌላዊ ኬዳም የስብከት መልዕክታቸውን ያቀረቡት ለበርካታ ዓመታት እንዳደረጉት ራሳቸው ያዘጋጁትን ስብከት በመስበክ አልነበረም። ይልቁንም እርሳቸው ጋሼ ሳህሌ የሚሏቸው የእምነት አባታቸው ለዓመታት ይሰብኩት የነበረውን በዮሐንስ 3:16 ላይ የተመሠረተ የደህንነት መልእክት ነበር ደግመው የሰበኩት።*

---------------------------//---------------------------

አቶ ሳህሌ እውነተኛ ወንጌላዊ ነበሩ። በየትም ስፍራ ተዘዋውረው ወንጌልን ለመስበክ ፈቃደኛ የነበሩ እኔ ገና ካመንኩበት ጊዜ ጀምሮ ለበርካታ ዓመታት ሳውቃቸው፣ ለመናገር እድል ሲያገኙ ሁል ጊዜ የሃያ ደቂቃ የደህንነት መልእክት ብቻ ያቀርቡ የነበረ ሲሆን በታማኝነትም ለዘመናት ይህንኑ የወንጌል ዋና መልእክት ሰብከዋል። ያመኑ እንዲጸኑም በትጋት እያስተማሩ በመንፈሳዊ ሕይወት ያሳድጉ ነበር። ወንጌላዊ ሳህሌ እኔ እና የእኛ አካባቢ ሰዎች ባመንን ጊዜ ለበርካታ ወራት ወደ መኖሪያ አካባቢያችን በየሳምንቱ ሐሙስ ሐሙስ እየመጡ የመንፈሳዊ እድገት ትምህርት አስተምረው ዛሬ ለደረስንበት ደረጃ እንድንበቃ መሠረት ጥለዋል። እኔ ገና በወንጌል አምኜ ቃሉን ለማወቅ እና ለማደግ እንድችል በውስጤ የተፈጠረውን ጥማት በማየት በትጋት ሊያሳድጉኝ የሚችለውን አቅጣጫ ያሳዩኝ ነበር።

ጋሼ ሳህሌ በበርካታ አጋጣሚ ለኔ በእዕሜ ዘመኔ ሁሉ ትምሕርት የሆኑኝን ነገሮች አቀብለውኛል። ያኔ እኛ በወንጌል አምነን አዳዲስ በነበርንበት ጊዜ አምልኮ በምናደርግባት ቤተ ክርስቲያን አንድ ሰው ነበር። ይህ ሰው ሁል ጊዜ የቤተ ክርስቲያናችን አምልኮ ስርዓት ሲያበቃ ይነሳና 'መልካም ምክር መከርኩ' ብሎ ሰዉን ሁሉ ክፉ እየተናገረ ይገስጻል። ሰው ሁሉ ደግሞ በሰውየው ንግግር እያዘነ ወደ ቤቱ ይሄዳል። በተደጋጋሚ ጥሩ ስብከት ተሰብከን ተምረን ልንወጣ ስንል ይቆምና የነበረውን መልካም መንፈስ የሚያጠፋ አላስፈላጊ ነገር ተናግሮ ሁላችንን ይረብሽናል። ይህ ነገር በጣም ሲደጋገም እኔንም በጣም ቅር ስላሰኘኝ እና መሽከም ስለከበደኝ አንድ ቀን ጋሼ ሳህሌን ‹‹ከዚህ ሰውዬ ጋር እንዴት አብሮ መኖር ይቻላል?›› ብዬ ጠየቅኳቸው። እርሳቸው ግን ‹‹ሰውን ስትወድ ከነ ክፉ ጸባዩ ውደድ፤ ሰውየውን እወደዋለሁ እያልክ በክፉ ጸባዩ የምትማረር ከሆነ ምኑን ወደድከው? ክርስቲያን ሰዎችን ሁሉ ክፉ ጸባይ ቢኖራቸውም እንኳን መወደድ አለበት።›› ብለው መከሩኝ። ደግሞም እራሳቸው ሰውየውን ምንም ክፉ ሳይናገሩ ፍቅር በማሳየት አስተማሩኝ። ይህም መሠረታዊ የሆነውን የክርስቲያን የፍቅር ግዴታ አሳዩኝ። ይኸው እኔም ከእርሳቸው ተምሬ እስከ ዛሬ ድረስ በነበሩኝ የአገልግሎት ዓመታት ማንንም ባህርይው ክፉ ብዬ አልሸሽም። ከእርሳቸው ለዕድሜ ዘመኔ የሚሆነኝን ትልቅ ትምህርት ተምሬያለሁ።

ሌላው ከጋሼ ሳህሌ የተማርኩት እና ሕይወቴን የለወጠው ትልቅ አጋጣሚ ደግሞ ያኔ እኛ ወንጌልን ካመንን በኋላ እነርሱ መጥተው በሕይወታችን ሊያሳድጉን በሚጥሩበት፣ ላመኑት ወገኖቻችንም በሚመሰክሩበት ወቅት በተደጋጋሚ ቤተሰብ ሆነው ሊጠይቁን

ወደ ቤታችን ይመላለሱ ነበር። በዚህ ጊዜ እኛ ለማስተናገድ ብለን ጠላ ወይም ሌላ መጠጥ ስናቀርብ ፈጽሞ "እኔ መጠጥ አልጠጣም" አይሉም ነበር። ከመናገር ይልቅም መጠጡን እንደሚጠጣ ሰው ተቀብለው ከጎን ያስቀምጡና ቀስ ብለው ሰው ሳያስተውላቸው ይመልሱታል። ከዚያም ውሃ ምናምን ጠይቀው ይጠጣሉ።

እኔም ይህን ድርጊታቸውን ሳይ ያኔ አምኜ የነበረ ቢሆንም መጠጥ መጠጣት አላቆምኩም ነበር። የእርሳቸውን ያለመጠጣት አቋም ስመለከት ግን "በቃ እኔም ከዛሬ ጀምሮ መጠጥ አቆማለሁ" አልኳቸው። እርሳቸው ግን "እኔን ስላየህ ብቻ አታቁም፤ ጉዳቱ ሲገባህ ነው ማቆም ያለብህ" አሉኝ።

የእውነትም የእርሳቸውን አለመጠጣት በማየት ያደረግኩት ውሳኔ ሊጸና አልቻለም። እንዳሉትም ከዚህ በፊት የምጠጣቸው አረቄ፣ ጠላና ቢርዬን ተራ በተራ ጉዳታቸውን በደንብ ስረዳ እና በራሴ ሲደርስብኝ ፈጽሞ መጠጣት አቆምኩ።

አረቄ መጠጣት የተውኩት እንዲህ ነበር። አንድ ጊዜ ቤታችን ውስጥ የተጠመቀ በጣም ብዙ አረቄ ቀኑን ሙሉ ከአንድ ወዳጄ ጋር ስጠጣ ውዬ ሰከርኩ። ከስካር የተነሳ ራሴን መቆጣጠር ስለተሳነኝም በድንገት ተነስቼ ወጣሁ። ከዚያም ከነበሩን ፈረሶች አንዱን ነጭ ትልቅ ፈረስ ይገፔ ኀበዝ ጋላቢ ስለነበርኩ ያገራችንን አውላላ ሜዳ በሽምጥ ግልቢያ አዳረስኩት። ከቆይታ በኋላ እኔም ፈረሱም ደክመን ስንመለስ ፈረሱ ሰውነቱ በሙሉ አረፋ በአረፋ ሆኖ ትንፋሹ እሩቅ ድረስ ይሰማ ነበር። ይህን ጊዜ እናቴ ባደርግኩት ነገር ተናደው ዱላ አንስተው እየተቆጡ ሲመጡ እኔ ከዚህ ቀደም አደርገው እንደነበር አክብሬያቸው መሸሼን ትቼ ምንም ሳልፈራቸው በድፍረት ቆሜ ጠበቅኋቸው። እርሳቸውም እጅግ በማዘን 'አሃ የኢየሱስ ሰው መሆን ለካስ እናትም ያስደበድባል' ብለው ዱላውን ጥለው ተመለሱ።

እርሳቸው ይህን ሲናገሩኝ ወዲያው ስካሬ ከላዬ ላይ ብን ብሎ ሲጠፋ ታወቀኝ። በጣም ተጸጸትኩ። ያመንኩትን ጌታ ስም እንዳሰደብኩም ገባኝ አዘንኩ። በዚያው ምሽትም ቀስ ብዬ ገብቼ እግራቸው ስር ወድቄ ይቅርታ ጠየቅሁ። አረቄም አዋራጅ መሆኑ ስለገባኝ ከዚያች ዕለት ጀምሮ በደረሰበት ሳልደርስ ወስኜ ከዚያ ወዲህ ወደ አፌ አስጠግቼው አላውቅም።

ጠላ መጠጣቴንም እንደ አረቄው ጉዳቱን ስላላየሁ ወስኜ ሳላቆም ቆየሁ። ሆኖም ጋሼ ሳህሌ እንዳሉት የጠላንም ጎጂነት የምረዳበት ቀን መጣ። አንድ ቀን ነጭ ልብስ ለብሼ ሠርግ ቤት ሄጄ ነበር። ሠርጉ ላይ የቀረበልኝን ጠላ ስጠጣ ውዬም ሞቅ ብሎኝ ከሠርጉ ቤት ወጣሁ። ወደ ቤቱ እየተመለስኩ እያለም አንድ ወንዝ ተሻግሬ ዳገት እየወጣሁ እያለ በጊዜው በነበረው ዝናብ የተነሳ ጨቅይቶ የነበረው ቀይ አፈር ላይ ከመጠጡ ሞቅታ ጋር ቀጥ ብዬ መሄድ አቅቶኝ ተንሸራትቼ ወደቅሁ። ከዚያም በጨቀየው ቀይ አፈር ላይ እየተንከባለልኩ ወንዙ ድረስ ወረድሁ። ስነሳ ለሠርግ የለበስኩት ሙሉ ነጭ የነበረ ልብስ ጭቃ በጭቃ ሆኖ ወደ ቡናማ ቀለም ተለውጧል።

በጣም ተበሳጭቼም አቅም ያሳጣኝን ጠላ ደግሜ እንደማልቀምስ ለራሴ እየማልኩ ወደ ቤቴ ገባሁ።

በስተመጨረሻም ብዙም አያስከርም የሚባለውን ቦርዴ እጠጣ ነበር። አንድ ቀን ግን የቦርዴንም ጎጂነት እንዲሁ አየሁ። በዚህ ጊዜ በእምነቴ እየበሰልኩ መጥቼ ነበር። ሆኖም አንድ ቀን ሰዎች በተሰበሰቡበት እኔም አብሬ ተቀምጬ ቦርዴ ቀርቦ እንጠጣ ነበር። ቦርዴው ለኔ ሲቀዳልኝ ተቀብዬ መጠጣት ጀመርኩ። በዚህ ጊዜ መንፈስ ቅዱስ መጠጣት እንደሌለብኝ እያሳሰበ ይወቅሰኝ ነበር። ሆኖም ጆሮ ዳባ ልበስ ብዬ በእምቢታ ስጠጣ ቆየሁ። ትንሽ ቆይቼ ግን ቦርዴው ሊስማማኝ አልቻለም። የጠጣሁት ቦርዴ ሽቅብ ሊወጣ ሲተናነቀኝ ቆይቶ ፋታ ሳይሰጠኝ እዚያው ባለሁበት በተሰበሰበው ሰው ፊት አስመልሶኝ አረፍኩ። በጣም አፈርኩ። እኔም ከዚያች ዕለት ጀምሮ ቦርዴም በሰው ፊት ስላዋረደኝ ይኸው እስከዛሬ ቀምሼው አላውቅም። ጋሼ ሳህሌ ጉዳቱ ይግባህ ያሉትም ደረሰ።

ጋሼ ሳህሌ መልካም የሕይወት ምሳሌ ከመሆን ባሻገር እኔ በደንብ ማንበብ እንድችል እና ትልቅ አገልጋይ እንደሆን በየጊዜው ልዩ ልዩ ትምሕርቶችን በማስተማር ድጋፍ ያደርጉልኝ ነበር። በጣም ትሁት ስለነበሩም አገልጋይ ትሑት መሆን እንዳለበት አሳይተውኛል። ጋሼ ሳህሌ ያኔ በሰይጣን አምልኮ ተተብትቦ በየቤቱ ዛር ያጓራበት የነበረውን የኛን ምድር ከሰይጣን እስራት ለማላቀቅ ወባ እና ተስቦ በሞላበት ሰው ወደ እኛ አገር መምጣት በሚፈራበት ዘመን ሳያቋርጡ እየመጡ በማገልገል እኔን ለአገልጋይነት እንድበቃ ብዙ ረድተውኛል። ከዚህም በኋላ እኔም ተራው ደርሶኝ ለወንጌል አገልግሎት ወደ ጌዴኦ ስሰማራ ጋሼ ሳህሌ አብረውኝ ነበር ወደ ጌዴኦ የዘመቱት። ሆኖም አገሩ ሊስማማቸው ስላልቻለ እስከመጨረሻው አብረውኝ በጌዴኦ ሊቆዩ ግን አልቻሉም።

------------------------//------------------------

# ምዕራፍ ፭

# የመጽሐፍ ቅዱስ ትምሕርት እና የአገልግሎት ጅማሬ

ጊዜው ከ1990ዎቹ ዓመታት አንዱ ነው። ወንጌላዊ ኬዳሞም አንተ የሚባሉባቸው ዓመታት አብቅተው አንቱታን ተጎናጽፈዋል። በኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ዋና ጽሕፈት ቤት ብሔራዊ ወንጌላዊ ሆነው በመላ አገሪቱ የሚገኙ ወንጌላውያንንና አገልጋዮችን ማሰልጠን ከጀመሩም ሰነባብተዋል። ከዚሁ አገልግሎት ጎን ለጎንም በቤተ ክርስቲያኒቱ ልዩ ልዩ ጉዳዮች ላይ የምክር አገልግሎት ለመስጠት ከቤተ ክርስቲያኒቱ መሪዎች (ዋና ጸሐፊዎች) ጋር ይዘዋወሩ ነበር። በዚህ ጊዜም ዱራሜ በመገኘት ከቤተ ክርስቲያን መሪዎች ጋር በመሆን በወቅቱ ተፈጥሮ ለነበረ ወቅታዊ ችግር እልባት ለመስጠት ለሦስት ቀናት ስብሰባዎችን አካሂደዋል። ይኸው ችግር ፈቺ ስብሰባ ሐሙስ ቀን ሲደረግ እስከ ሌሊቱ ዘጠኝ ሰዓት ረዝሞ የነበረ ሲሆን፤ ዓርብ ቀንም ስብሰባው ማልዶ በ12 ሰዓት እንዲጀምር ሁኔታዎች በማስገደዳቸው ወንጌላዊ ኬዳሞም በማለዳ ተነስተው ስብሰባው ላይ ተገኝተዋል። ሆኖም ቀኑ እየገፋ ሄዶ አራት ሰዓት ሲሆን ወንጌላዊው ቅዳሜና እሁድ በጋሞ (ጨንቻ) የነበረባቸው ኮንፍራንስ ላይ የመስበክ ኃላፊነታቸውን ለመወጣት ስብሰባውን አቋርጠው ሙሉጌታ አኖሬ ከተሰኘ የዋና ጽሕፈት ቤቱ ሾፌር ጋር ጉዞ ጀመሩ።

ወላይታ ሶዶ ከተማ ሲደርሱም በረጅም ስብሰባዎች የተዳከመ ሰውነታቸውን ለማሳረፍ በቀለ ሞላ ሆቴል አልጋ ለመያዝ ወሰኑ። እንዳሰቡትም ሆቴሉ ውስጥ ገብተው አልጋ ከጠየቁ በኋላ ድንገት "ከዚህ ግቢ ውጣ!' የሚል የመንፈስ ቅዱስን ድምጽ ሰሙ። ወደ ሾፌሩ ሙሉጌታ ዘወር ብለውም "ሙሉጌታ ና ውጣ ተባልኩ፤ ምን ይሻላል? ወደ የት እንሂድ?' አሉት። "ኤስ አይ ኤም ግቢ እንሂድ" አለ ሙሉጌታ። ኬዳሞም "ጥሩ ነው፤ እዚያ ገብተን ዛፍ ሥርም ቢሆን ብናድር ይሻላል" አሉና፤ ከተማው ጠርዝ ላይ ወደሚገኘው እና በቀደምቶቹ የኤስ አይ ኤም ሚሲዮናውያን ወደ ተቆረቆረው ኦቶና ግቢያ ተጓዙ።

ኦቶና (ጠረጴዛ) ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ቅጥር ግቢ ውስጥ እንደገቡ ሰዓታቸውን ሲያዩ ከቀኑ 6.00 ሰዓት ይላል። ወዲያውኑም በጊዜው ኦቶና ግቢ በኃላፊነት ይሠሩ

የነበሩት ሚሲዮናዊ ሚ/ር አዳምስ ብቅ አሉ:: ከወንጌላዊ ኬዳሞ ጋር ሰላምታ ከተለዋወጡ በኋላም ወንጌላዊው በጣም መድከማቸውን ገልጸው አልጋ ማግኘት ይችሉ እንደሆነ ጠየቁ:: ሚ/ር አዳምስም አልጋው እንደሚዘጋጅ ተናግረው ምሳ አብረዋቸው እንዲመገቡ ጋበዟቸውና ምሳቸውን በሚሲዮናዊው ቤት በልተው ለጊዜው የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ማደሪያ (ዶርም) ውስጥ ካሉ አልጋዎች በአንዱ ላይ ሊተኙ ገቡ::

ወንጌላዊው ጉናቸውን አሳርፈው ከቀኑ 10.00 ሰዓት ገደማ ከእንቅልፍ ሲነቁ ሁለት የመጽሐፍ ቅዱስ ኮሌጅ ሊማሩ አዲስ የገቡ ወጣት ሴት ተማሪዎች ሲጠብቋቸው አገኙ::

እነዚህ ተማሪዎች አንደኛዋ (አሰገደች የምትባል) ከይርጋ ጨፌ የመጣች ስትሆን ሌላዋ ደግሞ ከአዲስ አበባ ጎብረት አምባ አጥቢያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን የመጣች እህት ነበረች:: በወቅቱ እነዚህ ሁለት እንስቶች ለመጀመሪያ ጊዜ ከመኖሪያ ቀዬአቸውና ከቤተሰቦቻቸው ተለይተው ወደ ትምሕርት ቤቱ መምጣታቸው ስለነበረ እና አዲስ ሆነው በመጡበት ግቢ ነገሮች ከገመቱት በላይ አስቸጋሪ ስለሆኑባቸው ግራ ተጋብተዋል:: ስለሆነም በወንጌላዊ ኬዳሞ ፊት ቀርበው እያለቀሱ ያሉበትን አስቸጋሪ ሁኔታ እና የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ለመማር ብሎም ለማገልገል በነበራቸው ጥማት ዙሪያ የተጋረጠውን ፈተና ዘረዘሩላቸው::

ይኼኔ ወንጌላዊው ለምን ከበቀለ ሞላ ሆቴል ውጡ እንደተባሉ እና በደንብ ሊያርፉ እየፈለጉ ሁለት ሰዓት ብቻ ተኝተው እንደተነሱ ገባቸው:: ወዲያውም በ1943 ዓ.ም በሕይወታቸው የሆነውን ሁሉ ለሁለቱ እህቶች ይተርኩላቸው ጀመር::

በዚህ ጊዜ  ወጣቱ ኬዳሞ እንደዛሬ አንቱ የተባለ አገልጋይ ሊሆን ቀርቶ በክርስቶስ ኢየሱስ አምኖ ዳግም ከተወለደ እንኳን 10 ወራት አልሞላውም ነበር:: በእርግጥ ወንጌልን አምኖ ከተለወጠበት ጊዜ ጀምሮ ከእርሱ ቀድመው ካመኑት ጋር በመሆን የትውልድ መንደሩ ሻሸጎ እየተዘዋወረ እርሱ በክርስቶስ ኢየሱስ ያገኘውን አዲስ ሕይወት ለማካፈል ይዞር ነበር:: አንድ ወር ያህል በዚህ መልኩ ከቆየ በኋላም የእርሱን እና በአቅራቢያው ያሉ ቤተ ክርስቲያናትን የሚያስተባብረው ክፍለ ማኅበር ስብሰባ ላይ የመገኘት እድል ገጠመው:: በስብሰባው ላይ ከነበረው አጀንዳ አንዱም ክፍለ ማኅበሩ አንድ ሰው መጥቶ በቢቾ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት እንዲገባ ተሰጠው እድል የሚገባውን ሰው መወሰን ነበር:: በስብሰባው ላይ አቶ ኦርታቦ የሚባል ሰው እንዲገባ እንደተወሰነና እርሱ ግን ላለመግባት እያቅማማ እንዳለም ተነገረ:: በዚህ ጊዜ የያኔው አዲስ ክርስቲያን ኬዳሞ መሬት ለመሬት እየተንፏቀቀ ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ሽማግሌ ሄዶ እድሉ ለእርሱ እንዲሰጠው ተማጸነ:: በስብሰባው ላይም የትምህርት እድሉን አቶ ኦርታቦ አልቀበልም ካለ ለኬዳሞ እንዲሰጥ ተወሰነ:: ስብሰባው የተደረገው ቅዳሜ ቀን ስለነበርም እሁድ ቀን በጉዳዩ ላይ ለመወሰን ቀጠሮ ተይዞ የዕለቱ ስብሰባ አበቃ::

በቀጣዩ እሁድ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ለመግባት የቆረጠው ኬዳሞ የትምህርት መጀመሪያው ወቅት ደርሶ ስለነበር በዚያው ወደ ትምሕርት ቤት ለመሄድ ቅያሪ ልብስና ያለውን ጓዝ ሸክፎ ተመለሰ። ሆኖም የቤተ ክርስቲያኒቱ መሪዎች ካሉበት የሁለት ሰዓት መንገድ ርቀት ላይ የአንድ የቤተ ክርስቲያን አባል ቀብር ስለነበረ መሪዎቹ የግድ መሄድ እንዳለባቸው ተነጋግረው ሁሉም ወደ ስፍራው ተጓዙ። ከቀብር በኋላም በእንጥልጥል በቆየው ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ሰው የመላክ ጉዳይ ላይ ለመወሰን በለቅሶው ምክንያት ወደ ቤተ ክርስቲያን መመለስ ስላላመቻቸው የቤተ ክርስቲያን መሪዎቹ እዚያው ቀብር የተካሄደበት አካባቢ አንድ ጉብታ ላይ ለውሳኔ ተቀመጡ። ኬዳሞም ከጉብታው ዝቅ ብሎ ተቀምጦ የሚባለውን ጆሮውን ተክሎ ያዳመጥ ጀመር።

ይህን ጊዜ "ምን ይወሰን ይሆን?" በሚል ጉጉት ልቡ ክፉኛ እንደ ታምቡር ይደልቅ ገባ። በጊዜው ይላካል ተብሎ የነበረው አቶ ኦርታቦ ስለነበር የእርሱ 'እሄዳለሁ' ወይም 'አልሄድም' የሚል መልስ በኬዳሞ ሕይወት ላይ ታላቅ ለውጥ ያመጣ ነበር። ኦርታቦ ተጠየቀ። ይህን ጊዜ "መሄዱን እሄድ ነበር" ሲል ኬዳሞ በደስታ ተዋጠ። "ነበር" የምትለው ቃል አንዳች የምታስከትለው ነገር እንዳለ በመገመት። ኦርታቦ ቀጠለና "ነገር ግን የአስቴር እናት (ባለቤቴ) ታማለች። ማን ቤቱንና ከብቶቹን ይጠብቃል? አሁን መሄድ አልችልም " አለ። ኬዳሞም ካለበት በጥድፊያ ተነስቶ "እኔ እሄዳለሁ!' አለ፤ የሌሎቹን ውሳኔ ሳይጠብቅ። መሪዎቹም እንዲሄድ ፈቀዱ። ወዲያውም ለቅሶ ሊደርሱ ከወደ ሶዶ አቅጣጫ ከመጡ ሰዎች ጋር ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ጉዞ ጀመረ።

የተወሰነ ርቀት ተጉዘው አብረውት የሚሄዱት ሰዎች መንደር ሲደርሱም ማደር ግድ ሆነባቸው። ያቺ ሌሊት ለኬዳሞ በጣም ረዥም ነበረች። መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ገብቶ የእግዚአብሔርን ቃል የማወቅ ጥማት በውስጡ ይቀጣጠል ስለነበር እንቅልፍ በዓይኑ ሳይዞር ሌሊቱ አለፈ። ድንገት የእርግቦች ጉርምርምታ ሲሰማም "በቃ ሊነጋ ነው ልሂድ " ብሎ ተነሳ። አሳዳሪውም ሊሸኘው ተነስቶ ገና ጨለማው ሳይገፍፍ ጉዞ ጀመሩ። ሆኖም ጉዞው የተጀመረው ሌሊቱ ሳያበቃ ነበርና ገና ወፍ ሳይጮህ የኬዳሞ ታላቅ ወንድም የሚኖርበት ቃልሻ መንደር ደረሱ። ከዚህ በኋላም ኬዳሞ ከሸኚው ተለይቶ የወንድሙን ቤት አልፎ ወደ ሶቢቾ ገሰገሰ። ልክ ንጋት ሆኖ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት በር ማለዳው ላይ ሲከፈት ኬዳሞ የመጀመሪያ ሰው ሆኖ ተገኘ። ብዙ ሳይጉላላ ከራሱ የትውልድ መንደር (ሻሾጎ) የመጣ የራሱ ክፍለ ማኅበር ሰው አገኘና ነገሩን አስረድቶ ወዲያውኑ ተመዝግቦ ተማሪ ሆነ።

በትምህርት ቤት የመጀመሪያውን የ15 ቀናት ቆይታ አሳልፎም ለእረፍት እና ለትምሕርት ዝግጅት ወደ ቤት ሲመለስ ከከብቶቻቸው መካከል አንድ የደለበ ሰንጋ በሬ እንደተሰረቀ ተነገረው። ምንም ሳያደርግ የነበረውን የሁለት ቀን ቆይታ አጠናቅቆ እንደገና ወደ ትምህርት ቤት ተመለሰ። 15 ቀናት ያህል ቆይቶም ቀረብ ያለ ስፍራ

ወደሚገኘው ወንድሙ ቤት ሄደ። በዚህ ጊዜም እንደገና ከኬዳሞ ቤተሰብ ከብቶች መካከል መሰረቁን ለመናገር ወደ ኬዳሞ ወንድም ቤት ሰው ስለመጣ ኬዳሞ ቀድሞ ለምቶ ከወንድሙ የሚመጣበትን ቀጣ እና ድብደባ ፈርቶ የወንድሙን ቤት ጥሎ ኮብልሏል።

ኬዳሞ እንደገና ወደ ትምህርት ቤት ሄዶ እንደተለመደው 15 ቀናት ቆይቶ ለእረፍት ሲመለስ በእርሱ አለመኖር ምክንያት በከብቶቻቸው ላይ በየጊዜው በሚሆነው ነገር ያዘኑት እናቱ እሳት ለብሰው እሳት ጎርሰው ጠበቁት። የሚበላውን ቂጣና ወተት ከለጡት በኋላም ስለጠፉት ከብቶች የቤተ ዘመድ፣ የአገር ሽማግሌዎች ዘንድ ሰራቂዎቻቸውን ሊከሱ ሄደው የተባሉትን ነገሩት። በወቅቱ ሽማግግሌዎቹ "ያንቺ ልጅ 'እኔ ሌላ አገር አለኝ' ብሎ ጥሏቸው የሄደው ከብቶች ቢሰረቁ እኛ ምን ልናደርግልሽ እንችላለን?" ነበር ያሏቸው። የኬዳሞ እናትም ይህንኑ ለልጃቸው ነግረው ትምህርቱን እንዲያቆም በቁጣ አዘዙት። ኬዳሞ ግን በጄ አላለም። ይልቁንም እንዲህ ሲል ለእናቱ ጥያቄ አቀረበ፡- "እኔ ብሞት ከብቶቹን ምን ታደርጉኝዋላችሁ? የምትችሉትን አስቀርታችሁ ሌሎቹን ትሸጡ አልነበረምን?" በዚህ ግዜ እናትዮው ደንገጥ አሉ። ኬዳሞም ቀጠለና "በቃ ከዛሬ ጀምሮ እኔን እንደሞትኩ ቁጠሩኝ?' ብሎ ተነሳ። እናትየውም የሚመልሱትን አጥተው ዝም አሉ።

ወጣቱ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምሕርት ቤት ተማሪ ኬዳሞ ከዚህም በኋላ የሚማርባቸው ሁለት ዓመታት እስኪጠናቀቁ ከዘመድም ሆነ ከሌላ አቅጣጫ በርካታ ፈተናዎች ቢያጋጥሙትም በጽናት መክፈል የሚገባውን ዋጋ ሁሉ እየከፈለና ለቀጣይ የአገልግሎት ሕይወቱ ትምህርት እያገኘባቸው ተምሮ ጨረሰ።

ይህን ድንቅ ታሪክ የሰሙት ሁለቱ የሶዶ መጽሐፍ ቅዱስ ኮሌጅ አዲስ ገቢ ወጣቶች ራሳቸውን መቆጣጠር አልቻሉም። መሬት ወርደው በእምባ እየተራጩ "ከወንጌላዊ ኬዳሞ አንጻር እኛ ምንም አልደረሰብንም" በማለት በጌታ ፊት በምስጋና ተደፉ። ወዲያውም ሚ/ር አዳምስ መጡና ለወንጌላዊ ኬዳሞ ጥሩ አልጋ ወደ ተዘጋጀበት ሌላ ክፍል ወሰዷቸው። አሁን ጥሩ የሚያሳርፍ አልጋ ተገኙ።

ሆኖም ወንጌላዊ ኬዳሞ ጋደም ሊሉ እየሞከሩ ባሉበት «እኔ ነኝ አትፍሩ!» የሚለው የጌታ ድምጽ ያኔ ለሐዋርያቱ በተነገረበት ኃይል ወደ ልባቸው መጣ። ወዲያውም መተኛቱን ትተው በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 6 ላይ ያለውን በገሊላ ባህር የተፈጸመ ታሪክ እና የጌታን የማበረታቻ ንግግር አነበቡ። ባነበቡት መልዕክት ላይም "በሁኔታዎች ሁሉ ውስጥ የኢየሱስ አብሮ መሆን እና ውጤቱ" በሚል ርዕስ ጌታ ኢየሱስ አብሮን ሲሆን አስቸጋሪ የሆኑ ሁኔታዎች እንኳን እንዴት ሊታለፉና ሊለወጡ እንደሚችሉ የሚያስተምር መልዕክት አሰናዱ። ባዘጋጁት መልዕክት ውስጥም ሐዋርያቱ አስቀድመው እጅግ ድንቅ ተዓምር እንዳዩና በሁለት ዓሣና በአምስት እንጀራ 5 ሺህ ሰው ሲጠግብ ተመልክተው እንደተደቁ፤ ነገር ግን ጌታ ኢየሱስ ተጨማሪ ነገር ሊያስተምራቸው ማዕበልና ወጀብ በሞላበት ባህር በምሽት ለብቻቸው እንዲጓዙ

*እንዳደረገ፣ በኋላም በተጨነቁበትና ተስፋ በቆረጡበት ቅጽበት ደርሶላቸው «እኔ ነኝ አትፍሩ!» እንዳላቸው አተቱ። መልዕክታቸውንም "ዛሬ በማንኛውም ማዕበልና ወጀብ ውስጥ ላለን በዙሪያችን የሚታየን ሁሉ ድቅድቅ ጨለማ ለሆነብን ጌታ ኢየሱስ በአጠገባችን ካለ ሁሉን የሚያሸንፍ ሰላም አለን።" በማለት ደመደሙ።*

*ከዚህ በኋላ ይህን ድንቅ መልዕክት ወንጌላዊው ለበርካታ ዓመታት በአዲስ አበባ፣ በናዝሬት፣ በሆሣዕናና በሌሎች ከተሞች በቃለ ሕይወት፣ በብርሃነ ወንጌልና በሌሎችም አብያተ ክርስቲያናት በተደጋጋሚ ለብዙ ወገኖች ሰብከው ብዙዎች ተጽናንተውበታል። ግን ከሁሉም አስቀድሞ እርሳቸው ለቀጣይ አገልግሎታቸው ስብከት ሲያዘጋጁ በነበረበት ረፋድ ላይ ሁለት የሰዶ መጽሐፍ ቅዱስ ኮሌጅ ተማሪዎች ወንጌላዊው ወዳረፉባት ክፍል መጡ። ወንጌላዊ ኬዳሞንም በዚሁ ዕለት ምሽት ባለው የተማሪዎች የእንኳን ደህና መጣችሁ ፕሮግራም ላይ በኮሌጁ በመማር ላይ ላሉት ተማሪዎች በአጠቃላይ (በተለይም አዲስ ገቢ ለሆኑትና በነገሮች ተሸብረው ላሉት እንግዳ ተማሪዎች) የምክር ቃልና መልዕክት እንዲያቀርቡ እንደሚፈልጉ ነገሯቸው። ወንጌላዊውም በመንፈስ ቅዱስ ሥራ እየተደነቁ ፈቃደኛነታቸውን ገለጹ።*

*በምሽትም ያንን በመንፈስ ቅዱስ ምሪት ያዘጋጁትን መልዕክት ለተማሪዎች አቀረቡ። ተማሪዎች በጠቅላላም "እግዚአብሔር ተናገረን።" እያሉ በብዙ ደስታና በእምባ ጌታን እያመሰገኑ ጸለዩ። አንዳንዶች መሬት ወርደው እየተንከባለሉ ሁሉ በጌታ ፊት አነቡ፤ ትልቅ መጽናናትም ሆነላቸው።*

*እነዚያ በመጀመሪያ ወንጌላዊው ጋ ተስፋ ቆርጠው መጥተው ኬዳሞን ያናገሩ ሴቶችም የዚሁ ፕሮግራም ተካፋይ ነበሩ። ዛሬ ሁለቱም ተመርቀው ወደ መጡበት የአዲስ አበባና የደርጋ ጨፌ ቤተ ክርስቲያናት የተመለሱ ሲሆን የደርጋ ጨፌዋ በአሁኑ ወቅት የአካባቢው የሴቶች አገልግሎት አስተባባሪ ሆና በማገልገል ላይ ትገኛለች።*

---

## መጽሐፍ ቅዱስ ትምሕርት ቤት ገባሁ

እንግዲህ ዕድሉን አግኝቼ በታላቅ ጉጉት እና በደስታ ቦቢቾ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት በገባሁበት ወቅት የቦቢቾ ማዕከል ከመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ሌላ በርካታ ልዩ ልዩ አገልግሎቶች የሚሰጡበት የኤስ አይ ኤም ሚሲዮን ጣቢያ ነበር።

በጊዜው እኔ ጌታን የካቲት 4/1942 ዓ.ም ያመንኩ ሲሆን ቦቢቾ ትምህርት የጀመርኩት ጥቅምት 28/1943 ዓ.ም ነበር። በወቅቱ ትምህርት ለመጀመር ቦቢቾ ስገባ እኔ ከብዙዎች የወቅቱ ተማሪዎች ቡተለየ ማንበብና መጻፍ በደንብ ችዩ ነበር። ሌሎቹ ማንበብና መጻፍ ያልቻሉት በአካባቢያችን ትምህርትን ከማንበብ በላይ መማር ኃጢአት ነው ተብሎ ይታሰብ ስለነበር ነው። እኔ ግን ይህን አስተሳሰብ አልቀበልም ብዬ እሁድ

እሁድ ወደ እኛ ቤተ ክርስቲያን ለአካባቢያችን ወንጌልን የመሰከሩት እነ አቶ ሳህሌ ጆሴ ሲመጡ በአንድ ደብተር ላይ ፊደሎችን በሙሉ አስጽፋቸውና ከዚያ ሳምንቱን በሙሉ ፊደሎቹን መልሼ እየገለበጥኩ መጻፍ እለማመድ ነበር። ስለዚህም እኔ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ገብቼ መማር ስጀምር የመጻፍ ችግር አልገጠመኝም። አስተማሪዎቻችን በጥቁር ሰሌዳው ላይ እየጻፉ ሲያስተምሩን እኔ ከእርሳቸው እኩል ወደ ደብተሬ እገለብጥ ነበር።

እኔ ትምህርት ስጀምር ችግር ሆኖብኝ የነበረው የመጽሐፍ ቅዱሱ የእስራኤል ታሪክ ትምህርት ከመጀመሬ በፊት ጨርሶ ሰምቼው የማላውቀው ስለነበር ለኔ እንግዳ ነገር መሆኑ ነው። የሮሜ መጽሐፍን ስንማር መጽሐፉ በ15ቱ ምዕራፎች የሚያወራው ስለ እስራኤል መሆኑ እና ሮሜ በመጀመሪያ ከተማርኳቸው ትምህርቶች አንዱ ስለነበር ነገሩ ግራ ገብቶኝ ተጨንቄ ነበር። ከዚህም የተነሳ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት መጀመሬን መንገድ የሌለው ጥቅጥቅ ያለ ጫካ ውስጥ እንደገባሁ ቆጠርኩት። ስለሆነም ትምህርት የጀመርኩባቸው የመጀመሪያዎቹ አምስት ወራት በጣም አስቸጋሪ ሆነውብኝ ነበር። በጊዜው የምንማራቸው ትምህርቶች የሮሜ መልዕክት፣ ሐዋርያነት፣ የሉቃስ ወንጌል፣ የዓለም እና የቤተ ክርስቲያን ታሪክ፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችና የእስራኤል ታሪክ ነበሩ።

1. የሮሜ መልዕክትን የማስተማር ስጦታና የሥራ ትጋት ባላቸው አቶ ኤርጃቦ ሀንድሶ በሚባሉ አስተማሪ አማካኝነት የተማርን ሲሆን፤ በመልዕክቱ ውስጥ ያለውን ለዓለም ሕዝብ ሁሉ ስለተሰጠው ሙሉ መዳን፣ ከደህንነት እስከ አገልግሎት ድረስ ስላለው የክርስቲያን ኑሮ በስፋት አስተምረውናል።
2. የሐዋርያነት ትምህርት ስንማር ለአገልግሎት ስለመዘጋጀትና ስለ ቤተ ክርስቲያን አሠራር የተማርን ሲሆን ይህም ለእኔ ታላቅ የአገልግሎት መማሪያ ሆኖኛል። በኋለኛው ዘመኔም ይህንኑ ትምህርት "ሐዋርያነትና የመንፈስ ቅዱስ ሥራ" በሚል ርዕስ አሳትሜው በብዙ ቦታዎች አስተምሬዋለሁ።
3. የዓለምን ታሪክ ስንማር እግዚአብሔር በዘመናት ሁሉ ውስጥ ጥንት ከአዳም ጀምሮ እስከ ዛሬ የራሱን ሕዝብ ለመገናኘትና ከሰው ጋር አብሮ ለመሥራት የነበረውን መሻት ጨምሮ የሠራውን ሥራ ታሪክ ተምሬአያለሁ።
4. የሉቃስ ወንጌልን ስንማር የኢየሱስ ክርስቶስን ማንነት እና በሞቱና በትንሣኤው የተገኘውን የዘላለም ሕይወት መረዳት ችያለሁ።
5. ጥቅሶችን ስንማር 700 ያህል ጥቅሶች በቃላችን አጥንተን መጽሐፍ ቅዱስ በእጃችን ባንይዝ እንኳን ወንጌልን እንደሚገባ መመስከር እንድንችል ብቁ አድርጎናል።
6. የእስራኤልን ታሪክ ስንማርም የመንፈሳዊ ሕይወት አኗኗርና ጉዞ ምን መምሰል እንደሚገባው ተረድተናል።

## የሻሾነው ወይፈን

ይህን ሁሉ ትምህርት የተማርኩት በአንደኛው ዓመት የትምህርት ቤት ቆይታዬ ነበር። ይሁንና ያኔ ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ስገባ በክርስትና የአንድ ዓመት ዕድሜ እንኳን ያላስቆጠርኩ ነበርኩ። ይሁንና በ1943 ዓ.ም ጥቅምት 23 ትምህርት ከመጀመሬ በፊት ጥቅምት 8 ክርስቶስ ኢየሱስ ስለኔ ኃጢአት ሞቶ እንደተነሳ በማመን እኔም ለኃጢአት ሞቼ ከክርስቶስ ጋር አዲስ ሕይወት ማግኘቴን የውሃ ጥምቀት በመውሰድ መስክሬ ነበር። ትምህርት ቤት በነበረኝ የአንድ ዓመት ቆይታ ወቅት ያሳየሁት ባህርይ ግን ያልተለወጠና ከኃጢአት ያልተለየ ባህርይ ነበር። በእርግጥ እኔ መልካም ሰው ለመሆን እፈልግ ነበር። ሆኖም የቀድሞ ባህርዬ ሳይለወጥ የተለያዩ ኃጢአት የሆኑ ባህርያት ይታዩብኝ ነበር።

ካሳየኋቸው መልካም ያልሆኑ ባህርያት መካከል አንዱ ኃይለኛነት ነበር። አንድ ጊዜ እንዲህ አደረግሁ። አንድ ቀን የአስተማሪያችንን የማስታወሻ ደብተር ተራ በተራ እየተቀባበልን ማስታወሻውን ወደ ደብተራችን እንገለብጥ ነበር። በዚህ ወቅት ደብተሩን ወስዶ የመገልበጥ ተራው የአንድ አሳሮ የሚባል ልጅ ነበር። እኔ ግን ያኔ ትዕግስት ስላልነበረኝ ደብተሩን ከልጁ ጠረጴዛ ላይ በፈቃዱ ወስጄ መገልበጥ ጀመርኩ። በኋላ አሳሮ መጥቶ ደብተሩን ማን እንደወሰደ ሲጠይቅ ዝም ብዬ መጻፌን ቀጠልኩ። በኋላም እኔ ጋ መሆኑን አይቶ መጥቶ ሲያነሳው አመናጭቄ እንዳይወስድ አደረግሁት። በዚህ ጊዜ ይህን ያዩ አንድ በእድሜ የገፉ አብረውን የሚማሩ ሰው ሁለታችንንም ለቅጣት እንጨት እንድንፈልጥ አዘዙን። እንጨት እየፈለጥን እያለም አሁንም ተራ በተራ እየፈለጥን የእርሱ ተራ ሲደርስ መሥራት እንዳይችል ስለ ከለከልኩት በኃይል ሊነጥቀኝ ሲሞክር ገደል ውስጥ ከትቼ ረጋገጥኩት። ከዚያም እራሴ ከእርሱ ቀድሜ ሄጄ ለተማሪዎች ኃላፊ ከሰስኩት። አሳሮ ይህ ሁሉ ሲደርስበት እኔ ያደረግሁትን ያየ ምስክር ስላልነበር፣ የሚረዳው ሲያጣ ወደ ሰማይ እያየ «አዬ እግዚአብሔር!» አለ።

ይህም የኔን ልብ ክፉኛ ቢነካውም ምንም ሳላደርግ የምሽት ጸሎታችን ሰዓት ደርሶ የጸሎት ፕሮግራም ለመካፈል ተሰበሰብን። መጽሐፍ ቅዱስ ተነብቦ መዝሙር ዘምረን ወደ ጸሎት ልንሄድ ስንል እኔ በደል እያሰብኝ መጸለይ አልቻልኩምና እጄን አንስቼ በኃይል እያለቀስኩ አሳሮን ያደረግሁትን ሁሉ ተናዘዝኩ። በኋላም የትምህርት ቤቱ ማኅበረሰብ በጠቅላላ አስተማሪዎችና ተማሪዎች ተሰብስበው በእኔ ላይ የቅጣት ውሳኔ አሳለፉ። በኋላ ግን በወቅቱ አስተማሪያችን የነበሩት አቶ ኤርጃቦ በዚህ ትምህርት ቤት ቅጣት አይኖርም፣ በዚህ ላይም ኬዳሞን ብናባርር ለሻሾነ ጥሩ አይደለም ብለው ይቅርታ ተደረገልኝ።

ይህ ኃይለኛና መጥፎ ባህርዬን እግዚአብሔር እንዲለውጥልኝ ጸሎት ጀመርኩ። በቀን ሁለት ጊዜ በ7 ሰዓት እና በ10 ሰዓት አንዲት የብሳና ዛፍ ሥር ባለ ለምለም ሣር ላይ እየተንበረከክሁ እጸልይም ነበር።

በጊዜው በጣም ኃይለኛ ስለነበርኩ አብረውኝ የሚማሩ ተማሪዎች "የሻሾን ወይፈን[1]" ነበር የሚሉኝ። በኋላም እግዚአብሔር ጸሎቴን ሰምቶ ወይፈንነቴ ተቀይሮ ልዩ ኬዳም ሆንኩ። ተማሪዎችም "ወይፈኑ ተለወጠ" ይሉኝ ጀመር። ሁል ጊዜ አስተማሪ ወይም ተማሪ ‹‹ተው ተው›› ይለኝ የነበርኩት ሰው ተለውጬ ‹‹ተው›› የምባል መሆኔ ቀረ። ጭራሽ አስቸጋሪ መሆኔ ቀርቶ በሁለተኛው ዓመት የተማሪዎች ተወካይ ለመሆን በቃሁ። ልክ በቃሉ (በሮሜ. 7:14-25) እንደተጻፈው በእኔም ሕይወት ተመሳሳይ ነገር ሆነ። በፊት ለኔ ለኔ የምለው ሰው አዲስ ማንነት አግኝቼ ትሁት፣ ቸር፣ ፊጽሞ እኔነት ማይጎላበት ባህርይ ተላበስሁ።

## ‹‹በቃ እኔን እንደሞትኩ ቁጠሩኝ!››

ትምህርት በጀመርኩበት ዓመት የነበረብኝ ሌላው ችግር የቤተሰቤን ኃላፊነት መተዌ ያስከተለው ጉዳት ነበር። ሰይጣን እኔን ወደ ኋላ ሊመልሰኝ በተደጋጋሚ ከብቶቻችን እየተሰረቁ ቤተሰቦቼ የተቸገሩ ሲሆን ይህም እኔ ባለመኖሬ ምክንያት የተፈጠረ ችግር ስለነበር ትምህርቱን ትቼ እንድመለስ ብጣም ግፊት ያደርጉብኝ ነበር። ለመጀመሪያ ጊዜ በሬ ሲሰረቅብን ለእናቴ "በቃ እኔን እንደሞትኩ ቆጥራችሁ እኔ ሳልኖር ልትይዙ የምትችሏቸውን ያህል ከብቶች አስቀሩና ሌሎቹን ሸጡ።" ብዬ ነበር። ሆኖም በተደጋጋሚ ከብቶች ሲሰረቁ እኔ ችግር ይፈጠርብኝ ነበር። በአብዛኛው ከትምህርት ቤት በየአስራ አምስት ቀኑ ስመለስም "አሁን ደግሞ ምን ተፈጥሮ ይሆን?" እያልኩ እሰጋ ነበር።

አንድ ጊዜ እኔ ከትምህርት መልስ ከሻሾን የአራት ሰዓት ያህል መንገድ ርቀት ላይ ከሚገኝ መሬታችን ላይ የታጨደ ጤፍ ልወቃ ሄጄ ከታላቅ ወንድሜ ጋር አብሬ እሠራ ነበር። ጤፉን አሳድረን ቅዳሜ ልንወቃ እያዘጋጀን እያለ አንድ ዘመዴ ከሻሾን ሁለት አህዮቻችን መሠረቃቸውን ሊነግረን መጣ። በዚህ ጊዜ ሰውዬውን ከሩቅ ሳይ አቶ ባልቦ የመጣው "አንድ ችግር ቢኖር ነው" በማለት ሮጬ ሄጄ ስጠይቀው ሁለት አህዮቻችን መሠረቃቸውን ነገረኝ። እኔም ‹‹ወንድሜ እኔ እያለሁ እንዳይሰማ እስኪመሽ አትናገር›› ብዬው እስኪመሽ ሳይናገር ቆየ፤ እኔም ሲመሽ ቶሎ ከወንድሜ ሸሽቼ ሄድኩ። ሰውዬውም እኔ በሌለሁበት ነገሩን ለወንድሜ ሲነግረው ወንድሜ ተበሳጭቶ እኔን ሊደበድብ ቢፈልገኝም ሳያገኘኝ ቀረና እራሱ አህዮቹን ሊፈልግ ሄደ።

እኔም ወደ ትምህርት ቤት ተመልሼ ስማር ቆይቼ ወደ ቤተሰብ ለእረፍት ተመለስኩ። በዚህ ጊዜ ቤተሰቦቼ በሙሉ በቁጣ ተነስተውብኝ የኔ ትምህርት ያመጣባቸውን ችግር እየዘረዘሩ ይናገሩኝ ጀመር። እኔም ያኔ ለእናቴ የተናገርኩትን በመድገም "ያኔ በሬ በጠፋ ጊዜ ተናግሬያለሁ፤ እኔን በቃ እንደሞተ ሰው ቁጠሩና እራሳችሁ ልትጠብቋቸው የምትችሏቸውን ከብቶች አስቀሩ፤ ሌላውን ሸጡ" አልኳቸው። ሀሳቤን እንደማልቀይር

---

[1] ወይፈን ማለት በጉርምስና ዕድሜ ላይ የሚገኝ ከብት ሲሆን ኃይለኛ፣ ተዋጊ እና አመጸኛ በሬን ለመግለጽ ጥቅም ላይ የሚውል ቃል ነው።

ሲረዱም ተስፋ ቆርጠው ተዉኝ። ይህን ነገር እናቴ በጣም እንዳስበበት እና አቋሜ በደንብ እንደገባቸው ያየሁበት ጉዳይ ሆኖ አገኘሁት። ከብዙ ዓመታት በኋላ በደርግ ዘመን እኔ አዲስ አበባ እያለሁ ሰዎች እንደታሠርኩ ለእናቴ ሲያወሩላቸው በተናገሩትም ንግግር አረጋገጥሁ። በወቅቱ እናቴ ለሰዎች ያሉአቸው "ኬዳሞ ሞቻለሁ ያለው ድሮ ነው፤ አሁን ቢታሠር ምንም አይገርምም" ብለው ነበር።

ሐዋርያው ጳውሎስ በገላቲያ ምዕራፍ 2 ቁጥር 20 ላይ "ከክርስቶስ ጋር ተሰቅያለሁ፤ እኔም አሁን ሕያው ሆኜ አልኖርም፣ ክርስቶስ ግን በኔ ይኖራል፤" ብሎ የገለጸውን ያኔ እኔ ባላውቀውም መንፈስ ቅዱስ ግን ነገሩ በኔ ሕይወት እንዲፈጸም አደረገ፤ ክብር ለእግዚአብሔር ይሁን!!

## የሁለተኛ ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ቆይታዬ

ሁለተኛው ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ቆይታዬ የተለየና እኔ እራሴ አዲስና የተለወጠውን ኬዳሞ ያየሁበት ዓመት ነበር። መጽሐፍ ቅዱስ በ2ኛ ቆሮንቶስ ላይ «የእግዚአብሔር መንፈስ ባለበት ነፃነት አለ» እንደሚል እግዚአብሔር በቃሉና በመንፈሱ ባህርዬን ቀይሮ ከኃጢአተኛ ባህርይ ጋር መታገሌ ቀርቶ ሰላምና ደስታ የሰፈነበት ሰው ሁሉ "ተው" ሳይሆን "ነኸ" የሚለኝ፤ እኔ ሳልሆን ሌሎች ይቅደሙ የምል የሌሎችን እግር ሁሉ የማጥብ ሆንኩ። በኤፌሶን 2፡10 ላይ "መልካም ሥራ ለማድረግ በክርስቶስ ኢየሱስ ተፈጠርን" የሚለው በተግባር በሕይወቴ የታየበት ዓመት ነበር። ክብር ለእግዚአብሔር ይሁን!!

በዚያ ዓመት በነበረኝ የትምህርት ቆይታ ያስተማሩን አምስት አስተማሪዎች ሲሆኑ እነርሱም አቶ ኤርሻቦ፣ ሚስተር ዶናልድ፣ ሚስተር ከውዜር፣ አቶ አንጁሎ እና አቶ ደፋር ይባሉ ነበር። አቶ ኤርሻቦ በዚህኛው ዓመት 1ኛ ቆሮንቶስን፣ ኤፌሶንን እና የዮሐንስ ወንጌልን፣ ሚ/ር ዶናልድ ከዘፍጥረት እስከ ትንቢተ ኤርሚያስ፤ ገላትያ፣ 1ኛ ና 2ኛ ጢሞቴዎስ፣ 1ኛ ዮሐንስንና የስብከት አዘገጃጀትን አስተምረውናል። ሚ/ር ከውዜር ደግሞ የመጽሐፍ ቅዱስ አርእስታዊ ትምህርትን ሰጥተውናል። ይህም አንድ ርእስን በመምረጥ ከዚያ ርዕስ ጋር የሚያያዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን በመዘርዘር እያሳዩን የሚካሄድ ነበር። በእውነቱ እነዚህና በመጀመሪያው ዓመት የተማርናቸው ትምህርቶች እኔ ዲላ በነበረኝ የአገልግሎት ቆይታ እጅግ የተጠቀምኩባቸው እና በብቃት ለማገልገልም ያስቻሉኝ ናቸው።

አቶ ደፋር ታፈሰም የአማርኛ ንባብና ቃላትን ያስተማሩን ሲሆን ይህም ለመጪው ዘመን አገልግሎቴ በብዙ ጠቅሞኛል።

በዚህ ዓመት የጤና መታወክ አጋጥሞኝ የነበረ ቢሆንም ጌታ ይህንንም አስቸጋሪ ጊዜ በድንቅ አሳልፎኛል። ሕመም ያጋጠመኝ እንዲህ ነበር፦ የሁለተኛ ዓመት ትምህርቴን በመማር ላይ እያለሁ አንድ አናዬ የሚባል አብሮን የሚማር ተማሪ በሳምባ በሽታ

ይያዝና ወደ ቤቱ እንዲሄድ ተደረገ። ልጁ በሄደ ጊዜ እኔ አዝኜ በጣም አለቀስኩ። በኋላ ግን እኔ ራሴ ልጁ በሄደ ወር በማይሞላ ጊዜ ውስጥ የሳምባ በሽታ ይዞኝ እሰቃይ ጀመር። በሽታው ከባድ ስለነበረ በጣም ሲያሰቃየኝ ያየው ሚ/ር ዶናልድ የሚባለው አስተማሪያችን አንድ ምክር ለገሰኝ። "ወደ ቤትህ ሂድና ረጅም እረፍት ወስደህ ቅባት የበዛበት ምግብ፣ ሥጋ እና ማር በደንብ ብላ" አለኝ። በጊዜው እኔ በገንዘብም በኩል ሆነ በጎችና ማር እንደልብ ማግኘት እችል ስለነበር ፈረንጁ እንዳለኝ ለማድረግ ወደ ቤት ሄድኩ። በጊዜው ብዙ ሰዎች ይጸልዩልኝ ነበር። እኔም ሚ/ር ዶናልድ እንዳለኝ ወደ ቤቴ ሄጄ በደንብ በላሁ፣ ጠጣሁ። በኋላ በጣም ያሰለኝ የነበረው የሳንባ በሽታ ፍጹም ትቶኝ፣ ሐኪም ጋ ሄጄ ስመረመር ምንም በሽታ ሳይገኝብኝ ቀረ። እግዚአብሔር የብዙዎቹን የጸለዩልኝን ወገኖች ጸሎት ሰማ። እኔም ድኜ ወደ ትምህርቴ ስመለስ ከኔ በፊት የታመመው አናዬ በሐኪሞች እየተረዱ ቢቆይም ሕይወቱ አለፈ።

## የመጀመሪያ ስብከቴ

ከዚህ ሁሉ ባሻገርም በሁለተኛው ዓመት በቦቢቾ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ቆይታዬ ያገኘሁት አንድ ትልቅ ነገር የመስበክ ስጦታን ከእግዚአብሔር መቀበሌ ነበር። ይህን ስጦታ የተቀበልኩትና ጌታን ወደፊት ዕድሜዬን ሙሉ የማገለግልበት ስጦታዬ እንደሆነ ያወቅሁት የሁለተኛ ዓመት ትምህርታችንን በጀመርንበት የጥቅምት ወር ነበር። በትምህርት ቤታችን ተማሪዎች ያላቸውን የአገልግሎት ስጦታ ለመለየት እንዲቻል ለሁላችንም በየማለዳው የተማሪዎችና የመምህራን የጸሎት ፕሮግራም ላይ እንድንሰብክ ዕድል ይሰጡን ነበር።

አንድ ቀን ጠዋትም ተማሪዎችንና መምህራንን እንድሰብክ ተጠየቅሁ። እኔም ዘፍጥረት ምዕራፍ 1፡ 26-28፤ 2፡ 7 እና 15፤ 3፡ 1-9 ድረስ ባለው ሃሳብ ላይ ተመስርቼ እግዚአብሔር ሰውን በአምሳሉ እንደፈጠረው፣ ገዢ አድርጎ እንደፈጠረው፣ የራሱን የሕይወት እስትንፋስ እፍ ብሎበት እንደፈጠረው፤ ከዚያም አዳምና ሔዋን ከአንዲት ዛፍ ፍሬን እንዳይበሉ ቢታዘዙም እግዚአብሔር ያዘዛቸውን ትዕዛዝ ጥሰው ፍሬዋን እንደበሉና በኃጢአት እንደወደቁ፤ ይህም ሰውን ወደ ሞት፣ ከእግዚአብሔር ወደ መለየት፣ ከክብር ወደ መዋረድ፣ ከእግዚአብሔር ፊት ወደ መኰብለልና ወደ መደበቅ እንዳመጣቸው በመናገር የኃጢአትን ጎጂነትና አጥፊነት ሰበክሁ። በዕለቱ እግዚአብሔር የተለየ መልዕክት ለእኔም ሆነ ለሰሚዎች ተናገረ። እኔም ልክ እንደ ሌላ ሰው በደንብ ከተዘጋጀሁ እና ከጸለይሁ በኋላ የተለየ ሆኜ በእግዚአብሔር ጸጋ ሙሉ ኃይል ለብሼ እያለቀስኩ ሰበክሁ።

ይህንን ያዩት አስተማሪዎቼም ወዲያው በታህሳስ ወር ለአጠቃላይ የቦቢቾ ግቢ ሠራተኞችና የቀለም ትምህርት ተማሪዎች ጭምር በድጋሚ እንድሰብክ ጋበዙኝ። አሁንም በደንብ ጸልዬ እና ተዘጋጅቼ በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 8፡ 22-25 ላይ ባለው ጥቅስ ላይ ተመርኩዤ "ኢየሱስ በፍጥረታት ሁሉ ላይ ኃይልና ስልጣን አለው።"

በሚል ርዕስ ሰበክሁ። በቁጥር 24 ላይ "እርሱም ነቅቶ ነፋሱንና የውሃውን ማዕበል ገሰጻቸው፤ ተዉም" ይላል። እኔም 'ያቃተንን ነገር ሁሉ ወደ ኢየሱስ እናቅርብ እርሱ ኃይል አለው።' እያልኩ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል እሰብክ ነበር። የዚህን ዕለት መልዕክት የሰሙ ሰዎች ተደንቀው ለብዙዎች ነገሩ። አንዳንዶችም ከቤተ ክርስቲያናችን ቀደምት አባቶች አንዱና የወንጌል አርበኛ የሆኑት አባ ጉሴ ያሉበት ቤተ ክርስቲያን (ዱባንቾ) ሄደው ተናገሩና ከ1 ወር በኋላ ወደዚያ ሄጄ እንዳገለግላቸው ጠየቁኝ። አንድ ወር ሙሉ በኃይል ጸለይኩ። ምክንያቱም የዱባንቾ ቤተ ክርስቲያን በዚያ ጊዜ እነ አባ ጎሴን የመሳሰሉ ታላላቅ ሰዎች የነበሩባት የመጀመሪያዋ የከምባታ እና ሃዲያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ነበረች።

ከዚያም በደንብ ተዘጋጅቼ በመሄድ በኢሳይያስ ምዕራፍ 14 ከቁጥር 12-23 ያለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል መሠረት አድርጌ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል በሰይጣን ልብና ሀሳብ የነበረውን የባቢሎንን መንግሥት አወዳደቅ በማሳየት እና የሰይጣንን አወዳደቅ የሚያመለክተውን ሀሳብ መሠረት በማድረግ ትዕቢት ሰውን የሚያዋርድ እና የሚጥል መሆኑን ሰበክሁ። በዚህ ጊዜ ሰው ሁሉ ልቡ ተነክቶ አንዱ በአንዱ እግር ላይ እየወደቀ እያለቀሰ ንስሃ ይገባ ነበር። በጣም ድንቅ ጊዜ ነበር። ከዚህ ስብከቴ በኋላ ሰዎች እኔን እያደነቁና እያመሰገኑ ሲናገሩ ከኔ አገር የመጡ አንዳንዶች "የኛ አገር ልጅ ነው" እያሉ በኩራት ሲናገሩ ላይ፤ ምንም ስለ ትዕቢት አዋራጅነት ስሰብክ የቆየሁ ቢሆንም የኔም ልብ መታበይ ጀመረ። ይህ እንግዲህ መድረክ ላይ ቆሜ መስበክ ከጀመርኩ ገና ሦስተኛዬ ነበር።

## በራስ የመደገፍ ውጤት

ወዲያውም በዱባንቾ የሰበኩትን ስብከት የሰሙ ሰዎች ሌላ ቦታ ሄደው ስለ አገልግሎቴ ተናገሩና የሦስት ቀን ኮንፍራንስ የተዘጋጀበት ቦታ ላይ 5 ጊዜ መልዕክት እንዳቀርብ ወደ ሌላ አካባቢ ተጠራሁ። ከዚህ ቀደም በነበሩኝ አገልግሎቶች በብዙ ፍርሃት እና መንቀጥቀጥ እግዚአብሔር እንዲረዳኝ እና መልዕክት እንዲሰጠኝ በመጸለይ በእግዚአብሔር ጸጋ ተደግፌ አገለግል ነበር። በዚህ ግን ልቤ በትዕቢት ተሞልቶ እንደበፊቱ እንደማሳካልኝ ልቤ ተማምኖ ነበር። ከዚህ በፊት በሰበክሁኝ ቁጥር ብዙ ጸልዬ እቆም ስለነበር እግዚአብሔር ይሠራ ነበር። በአሁኑ ግን በራሴ ተማምኜ በራሴ ስብከት አዘጋጅቼ ብዙ ሳልጸልይ ወደ ተጠራሁበት ስፍራ ሄድኩ።

ኮንፍራንሱ ቦታ ደርሼ በኮንፍራንሱ የመጀመሪያ ቀን እኔ የማገለግልበት ጊዜ ደርሶ መድረክ ላይ እስክቆም ድረስ ልቤ ሙሉ ነበር። ልክ መድረኩ ላይ ቆሜ ስብከቴን ማቅረብ እና መናገር ስጀምር ግን ባዶ ቆርቆሮ ሆኜ ነበር። ብጮህ ብጮህ ምንም ጠብ የሚል ነገር አልነበረም። የምናገረው እንኳን ለሚሰሙኝ ለኔ ለራሴ ምንም ፍሬ ነገር ያለው ሆኖ የሚሰማ አልነበረም። በኋላም ጮኼ ጮኼ ጨረስኩና ልክ ሰርቆ እንደተያዘ ሌባ በመሳቀቅና በኃፍረት ከመድረኩ ወርጄ ለኔ ማረፊያ እንዲሆን ወደ

ተሰጠኝ ጎጆ ቤት ሄጄ በደረቴ መሬቱ ላይ ተዘርሬ ማልቀስ ጀመርኩ። ወዲያውም "እግዚአብሔር ሆይ ክብርህን ወስጃለሁና ማረኝ" በማለት እያለቀስኩ ጸለይኩ። ኃጢአቴንም ስናዘዝ በራሴ ምንም ሳደርግ እንደማልችል ከዚህ ቀደምም በኔ የሠራው እግዚአብሔር እንደነበር ገባኝ። እንደገና ንስኃ ገብቼ እግዚአብሔር እንዲረዳኝ ለመንኩት።

እግዚአብሔርም መሐሪ አምላክ ነውና ፊቱን ወደ እኔ መለሰ። ከዚያ በኋላ የነበረው ቀሪ ስብከቴም ሕይወት ያለበት ሆነ። ይህ ስብከት በጀመርኩባቸው የመጀመሪያ ወራት የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ተማሪ እያለሁ ያጋጠመኝ ነገር እስከዛሬ ድረስ ለኔ ትልቅ ትምህርት ያገኘሁበት በጣም ጠቃሚ ወቅት ሆኖ አለፈ። ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ማንም ቢያደንቀኝ ምንም ያህል ታላቅ ስብከት ብሰብክና ብዙ በረከት ቢገኝበት እኔ "የሠራው እግዚአብሔር ነውና ክብሩ ለእግዚአብሔር ይሁን" እያልኩ ከሰዎች ምስጋና እሸሻለሁ። ይኼም ለኔ ትልቅ በረከት ሆነልኝ። ክብርና ምስጋና ለእግዚአብሔር ይሁን!!

ሌላው በቦቢቾ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት እያለሁ ያገኘሁት ልምድ የመጀመሪያ ዓመት ተማሪ እያለሁ እና በ1944 ዓ.ም ትምህርት ካለቀ በኋላ ሻሾን ስመለስ ከሰኔ እስከ መስከረም ባሉት ወራት አዋቂዎችንና ሕፃናትን እየሰበሰብኩ ፊደል ቆጠራ፣ ንባብና መጽሐፍ ቅዱስ አስተምር ነበር።

በዚህ ዓይነት እግዚአብሔር የቦቢቾ መጽሐፍ ቅዱስ ተማሪ የነበርኩባቸውን ዓመታት በትምህርት እና በአገልግሎት ልምምድ ብሎም በመንፈሳዊ ማንነቴ አድጌ ሙሉ ሰው እንድሆን እና ለአገልግሎት ብቁ እንድሆን አዘጋጀኝ። ክብር ለስሙ ይሁን!!

## ብዙነሽን መተዋወቅ (አፍላው ፍቅር እና የትዳር ዱብ ዱብ)

በዚሁ የተማሪነት ዘመኔም ለእኔ እንደ መንፈሳዊ አባት ሆነው ወደ ጌታ እንድመጣ እና በመንፈሳዊ ሕይወቴ እንዳድግ የረዱኝ አባቴ አቶ ሳህሌ የእኔን የወደፊት የአገልግሎት ዘመን አስቀድመው አይተዋል። ለአገልግሎቴ ውጤታማነት በማሰብ ለወደፊት ሚስት ልትሆነኝ የምትችል ብለው ያሰቧትን አማኝ እህት ወደ እኔ ላኩ። ብዙነሽ አኖሌ ከኔ የትውልድ መንደር ትንሽ ፊቀቅ ብሎ ያለ አካባቢ ትኖር ነበር። አቶ ሳህሌ እንደነገርኳችሁ በአካባቢያችን በሁሉ ዘንድ እንደ መንፈሳዊ አባት የሚታዩ በጣም አስተዋይ ታላቅ የወንጌል አገልጋይና የእኛን አካባቢ ቤተ ክርስቲያናትን ከተከሉ አባቶች አንዱ ነበሩ። ስለሆነም በጊዜው ወንጌሉን ካመኑ ወጣት ሴቶች አንዷ የነበረችው ብዙነሽ የእኔ የትዳር አጋር እንድትሆን በማሰብ እኔ እንድተዋወቃት ነበር ወደ እኔ የላኩአት።

ብዙነሽ አንድ ቀን እኔ እማርበት የነበረው መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት መጥታ ስንገናኝ በወቅቱ እኔ ምንም እንኳን የትዳር አጋሬ ከመሆን የሚያግዳት እንከን

ባላገኘባትም በተገናኘንበት እና በተዋወቅንበት የመጀመሪያዋ ዕለት እርሷን ስለማግባት አለማግባቴ አልወሰንኩም ነበር። ይልቁንም በሌላ ቀን እኔ እርሷ ወዳለችበት አካባቢ ሄጀ ላገኛት ቀጠሮ ይዘን ተለያየን። ይህም በትምህርት ቤት ቆይታዬ ወቅት ከተፈጠሩት ታላላቅ ጉዳዮች አንዱ ሲሆን በቀጣዩ የሕይወት ዘመኔ ሊመጣ ያለ አንድ ታላቅ ምዕራፍ ጅማሬ ነበር።

# ምዕራፍ ፯

# የወንጌል ጥሪ እና ዘመቻ ጌዴኦ

ወጣቱ ኬዳሞ በክርስቶስ ኢየሱስ አምኖ ከዳነ በኋላ በውስጡ የተፈጠረውን እግዚአብሔርን የማወቅ ጥማት ለማርካት መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ከገባ አንድ ዓመት አልፎታል፡፡ በትምህርት ቤቱ በነበረው ቆይታ መጽሐፍ ቅዱስን እየተማረ ቃሉ እውቀት እና በሕይወቱም እግዚአብሔርን ወደ መምሰል ማደግ ጀምሯል፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ገብቶ ለመማር ሲወስን ትምህርቱንም ሳያቋርጥ ለመቀጠል ብዙ ዋጋ መክፈል አስፈልጎታል፡፡ ይሁንና የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቱን አጠናቅቆ ሕይወቱን እንዴት መምራት እንደሚገባውና ምን ማድረግ እንዳለበት ግን ገና አልወሰነም ነበር፡፡

የሁለተኛ ዓመት ትምህርቱን በጀመረ በአንድ ወሩ (በ1944 ዓ.ም ኅዳር ወር) የሚማርበት ቦቢቾ ታላቅ ኮንፍራንስ ተደረገ፡፡ በጊዜው በስብከት የሚያገለግሉት ከካናዳ የመጡ አገልጋዮች ሲሆኑ በተለይም ሚስተር ራስ ላፍ የተባለ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የተሞላ ድንቅ ሰባኪ ከነበሩት አገልጋዮች መካከል ይገኝ ነበር፡፡ በዚህ ኮንፍራንስ ላይ ታላቅ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል በኮንፍራንሱ ተካፋዮች ላይ ወርዶ ነበር፡፡ ኬዳሞም በዚሁ ኮንፍራንስ ላይ የወረደው የመንፈስ ቅዱስ መገኘት የልቡን በር በኃይል ያንኳኳ ለነበረ በድንገት ልቡ በክርስቶስ እና በመስቀሉ ፍቅር ሲቀልጥ ይሰማው ጀመር፡፡ ይህ ለሚሰማው ጥልቅ የፍቅር ስሜት ምን ምላሽ መስጠት እንዳለበት አስጨነቀው፡፡ በዚያ ዘመን ከፍ ያለ ዋጋ ያለው ሊባል የሚችለውን በኪሱ የነበረ አራት ብር አውጥቶ ለጌታ ቢሰጥም በውስጡ የተቀሰቀሰው ጥማት፣ ፍቅርና ረኃብ ግን በዚህ ብቻ የሚረካ አልነበረም፡፡

ስለዚህ ኬዳሞ ካለው ንብረት በሙሉ ለጌታ ቢሰጠው ደስ የሚሰኝበት የውስጡን ጥማት የሚያረካው ምን እንደሆነ አሰበ፡፡ ወዲያውም በቤቱ ያለችውን በጣም የምትወደውንና እርሱም የሚወዳትን ጊደር አሰበ፡፡ ለጌታ ለመስጠትም ቃሉን ሰጠ፡፡ ነገር ግን ይህም በውስጡ የተቀጣጠለውን የፍቅር እሳት ሊያበርደው አልቻለም፡፡

ወዲያውም በዚያ ጉባኤ ላይ በኃይል ወርዶ ብዙዎች ራሳቸውን ሁሉ እንዲሰጡ ሲናገራቸው የነበረው የእግዚአብሔር መንፈስ ራሱን እንዲሰጥ ሲጠይቀው ተሰማው፡፡

*ኬዳሞም ወዲያውኑ የፍቅር እንባውን እያፈሰሰ ተነስቶ ራሱን ለጌታው ሰጠ። ያን ጊዜ በጌታ ፍቅር እና ጌታን ደስ በማሰኘት ጥማት የተቀጣጠለው እሳት በርዶ ታላቅ ደስታና ሰላም በልቡ ሞላ። ወዲያውም የኮንፍራንሱ አዘጋጆች የኬዳሞን እና የሌሎችን ራሳቸውን እና መላ የሕይወት ዘመናቸውን ለጌታ ሊሰጡ የወሰኑ ሰዎች ስም መዝግበው ያዙ። ኬዳሞም ራሱን ለወንጌል አገልግሎት በመለየት በተጠራበት ዓላማ ለመጽናትም ይጸልይ ጀመር።*

## የአገልግሎት ጥማት እና ጽኑ ቃል ኪዳን

እራሴን ለጌታ ሥራ የሰጠሁት እና በግልጽ የወሰንኩት ከላይ በተጠቀሰው ቀን ቢሆንም በተለያዩ ጊዜያት የጌታ የወንጌል አደራ ባለዕዳነቴ እንዲሰማኝ የሚያደርጉ አጋጣሚዎች ብዙ ነበሩ። ከላይ የተረክሁት የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ቆይታዬም ለጌታ የተለየሁ እንድሆን በብዙ አቅጣጫ አስተምሮኛል። በተለይ አንዳንድ ከትምህርታችን ጋር የተያያዙ ሁኔታዎች ራሴን ሙሉ ለሙሉ ለጌታ እንድሰጥ ያሳሰቡኝ ነበር። ለምሳሌ ያህል በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት እያለን ተማሪዎች የምንመገበውን ምግብ የምናገኘው የከምባታና ሃዲያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያናት ምዕመናን እንደ ገብስና አተር ያሉ ልዩ ልዩ የእህል ዓይነቶችን እና ያልተጋገረ ቆሎ ያመጣሉ። እኛም ቆሎውን እየጋገርን እህሉን ንፍሮና ቆሎ እያደረግን እንመገብ ነበር። በእርግጥ ገና ስጀምረው ይህ ምግብ ለኔ በጣም አስቸጋሪ ነበር። ምክንያቱም በቤቴ እያለሁ ቅቤና ወተት እንደልብ አገኝ ስለነበር ቅቤ ወይም ወተት ያልፈሰሰበት ቆሎና ደረቅ ምግብ ጨርሶ አልበላም ነበር። ነገር ግን ጌታ ሁሉን በደስታ መመገብ እንድችል አደረገኝ። ስለዚህ እነዚህ ምዕመናን በልግስና የሚሰጡትን ምግብ ስመገብ ከፍ ያለ የባለዕዳነት ስሜት ይሰማኝ ነበር።

አንድ ጊዜ ገና የመጀመሪያ ዓመት ተማሪ እያለሁ አንድ ሰው ተቆርጦ የተዘጋጀ ቆሎ በትከሻው ተሸክሞ ረጅም ርቀት ተጉዞ መጣ። ሰውዬው እኛ ጋ ደርሶ ቆሎውን ከትከሻው ሲያወርድ ላቡ ከሰውነቱ እንደ ውሃ ይንጠባጠብ ነበር። «ከየት ነው የመጣኸው?» ብዬ ስጠይቀው ዋራሞ ከሚባል ቤተ ክርስቲያን ብሎ መለሰልኝ። ዋራሞ የ4 ሰዓት የእግር መንገድ ያህል የሚርቅ ቦታ ነበር። ወዲያው ለራሴ "ይህን ቆሎ በልቼ ተምሬ ጌታን ባላገለግል የዚህ ሰው የላብ ዕዳ ይኖርብኛል" ብዬ አሰብኩ።

ይህም ብቻ ሳይሆን ትምህርት በጀመርንበት ወቅት የነበረው የምግብ ሁኔታ በጣም አስቸጋሪ ስለነበር ይህን ያዩት ሚ/ር ዶናልድ ነገሩን ገልጸው ካናዳ ለሚገኙ ቤተ ክርስቲያናት ጻፉና ወዲያው የገንዘብ እርዳታ ተልኮ ነገሮች ተስተካከሉልን። አንድ ቀን ሚ/ር ዶናልድ በክፍል ውስጥ እያስተማሩን እያለ ነገሩ ጥያቄ ይፈጥርብኝ ስለነበር "ይህንን ገንዘብ የሚልኩልን ሰዎች ብሩን ከየት እያመጡ ነው የሚረዱን?" ብዬ ጠየቅኋቸው። እርሳቸውም "በካናዳ የሚገኙ ሰዎች ልዩ ልዩ ሥራ እየሠሩ ከሚያገኙት ገንዘብ ላይ የሚልኩ ሲሆን አንዳንድ ጊዜ አንዳንዶች ገንዘብ ሲያጡ ወደ ሆስፒታል

ሄደው ደማቸውን በመሸጥ የሚያገኙትን ገንዘብ ይልካሉ" አሉኝ። እኔም ይህንን ስሰማ "በክርስቶስ ኢየሱስ ደም የተገዛሁበት ዕዳ ላይ የሰዎች የደም ዕዳ ተጨምሮበት የዚህ ሁሉ ደም ባለ ዕዳ ሆኜ እንደሚገባ ባላገለግለው ወዮልኝ!" አልኩ።

በእርግጥ እኔ ቦቢቾ ተማሪ በነበርኩባቸው ዓመታት በተለይ በስተመጨረሻ የሚያስፈልገኝን ቆሎ፣ ቅቤ፣ እና እህል ሁሉ ከእናቴ ጋ እያስመጣሁ አንዲት አዳ የሚባሉ ሞግዚት ነበሩኝና እርሳቸው እያዘጋጁልኝ እመገብ ነበር። አንዳንዴ ሌሎች ጓደኞቼንም እየወሰድኩ አብረን እንበላ ነበር። እኚህ እናት እኔን ከመርዳት ባለፈም እናቴን መስክረው ወደ ጌታ ያመጡ ታላቅ ሴት ናቸው።

እንግዲህ በዚህ መልኩ እግዚአብሔር አዘጋጅቶኝ እና የወንጌል አደራውን አሸክሞኝ ለወንጌላዊነት ሥራ ብቁ ሆኜ ከቦቢቾ ወጣሁ።

በብዙ ሁኔታ ውስጥ አልፌ ለወንጌላዊነት ከመዘጋጀቴ ባሻገርም የክርስቶስ የማዳን የምስራች ወንጌል ሰባኪ ሆኜ ማገልገል እንዳለብኝ ያስገነዘበኝ ሌላው ጉዳይ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት የመጀመሪያ ዓመት ትምህርት እንደጀመርኩ ያገኘሁት እውቀት ነበር። በዚህ ጊዜ የሮሜ መጽሐፍን ስንማር ከምዕራፍ 1-5 ባሉት ምዕራፎች ላይ ለሰዎች ሁሉ የሚሆን መዳን እና ጽድቅ በኢየሱስ ክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ በኩል እንደተገኘ ተማርን። ይህንን ታላቅ የምሥራች ለሰዎች ሁሉ የማድረስ ኃላፊነትም በእኛ ላይ እንደወደቀ ስረዳ ታላቅ ዕዳ እንዳለብኝ ተገንዝቤ ስለነበር በብዙ እምባም ይህን ዕዳዬን ሳልከፍል እንዳልቀር እጸልይ ነበር።

ስለዚህም ልክ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቴን እንደጨረስኩ በመኖሪያ ቤታችን ደጃፍ ሁል ጊዜ ጠዋት ከ2 ሰዓት እስከ 5 ሰዓት ድረስ ልጆችን፣ አዋቂ ሴቶችና ወንዶች እየሰበሰብኩ አስተምር ጀመር። ብዙ ሰዎች እየተሰበሰቡም ማንበብና መጻፍ እንዲሁም የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት (ሉቃስ ወንጌልን) ሜዳ ላይ ተቀምጠው አስተምራቸው ነበር። ይህ ግን እኔ በውስጤ ከነበረው የስብከት ወንጌል ጥማት የተነሳ ያደረግሁት ቢሆንም ሁሉንም ወገን የሚያስደስት አልነበረም።

የቤተ ክርስቲያናችን ሽማግሌዎች "ኬዳሞ በራሱ ደጃፍ ጸሎት ቤት ሊተክል ነው" ብለው እንደ ተቃወሙኝ ስሰማ ነገሩን አስቂኝ ሆኖ አገኘሁት። ምክንያቱም እርነሱ የክርስቶስ አገልጋዮች እንደመሆናቸው በአንድ ቀን ሺህ ቤተ ክርስቲያን ቢተከል ለይጣንን እንጂ እነርሱን ሊያስከፋቸው አይገባም ነበርና። በጊዜው እነርሱ ሀሳብ የሆነባቸው የሥልጣንና የመሪነት ጉዳይ ብቻ ነበር እንጂ ስለወንጌል መስፋፋት ስራእይ ሆነው አልነበረም። እኔ ደግሞ በደጃፋችን ወንጌል መስበክ የጀመርኩት ያኔ ጸሎት ቤታችን የተሠራው ሕዝቡ ከሚኖርበት አካባቢ የአንድ ሰዓት መንገድ ያህል ርቆ ገለል ያለ ቦታ ላይ ስለነበር ነው። ስለሆነም እኔ ከጸሎት ቤቱ የ40 ደቂቃ ያህል መንገድ ርቆ በሚገኘው የኛ ቤት ደጃፍ ላይ ትምህርቱን ጀመርኩና ብዙ ሕዝብ እየተሰበሰበ ይማር ጀመር። ይሁንና ቢፈቅዱም ባይፈቅዱም ሽማግሌዎችን ሳላስፈቅድ

ትምህርቱን መጀመሬ ስህተት ነበር። ስለዚህ ትምህርቱ በዚህ ምክንያት በኛ ደጃፍ መካሄዱ ቀርቶ ወደ ቤተ ክርስቲያን እየሄድኩ ማስተማር ጀመርኩ። በጊዜው በኛ ደጃፍ የነበረውን ያህል ብዙ ሕዝብ ባይመጣም የመጡትን ጥቂት ሰዎች እያስተማርኩ እግዚአብሔር ወንጌል የምሰብክበትን የአገልግሎት በር እንዲከፍትልኝ በኃይል እጸልይ ነበር።

## የጸሎቴ መልስ

በሻሾን ወንጌል ለመስበክ የራሴን ጥረት እያደረግሁ ብቆይም በውስጤ የተፈጠረው ከፍተኛ የባለ ዕዳነት ስሜት ግን ፈጽሞ አልበረደም። ስለዚህም ከቦቢቾ ተመርቄ ከወጣሁ ጀምሮ ጌታ የወደፊት አቅጣጫዬንና የአገልግሎት መስኬን እንዲያሳየኝ በኃይል እጸልይ ነበር።

በዚህ ሁኔታ ውስጥ እያለሁ በ1944 ዓ.ም ሐምሌ ወር አንድ አርብ ማታ እያለቀስሁ ስጸልይ አደርኩ። ሐሙስ ማለዳ ከብቶች ከበረት አስወጥቼ ሜዳ ላይ ሲተኙ ወደ አንድ ሰዋራ ቦታ ገባሁና ጸሎት አድርጌ መጽሐፍ ቅዱሴን ስከፍት ኤርምያስ ምዕራፍ አንድን ገለጥሁ። ምዕራፉን እያነበብኩ ሄጄ ቁጥር 7 ላይ "ወደምስድድህ ሁሉ ዘንድ ትሄዳለህና፣ የማዝዝህንም ሁሉ ትናገራለህና ብላቴና ነኝ አትበል" የሚለው እግዚአብሔር ለኤርምያስ የተናገረው ቃል ጋ ስደርስ ጌታ በቀጥታ ለእኔ እንደተናገረኝ በልቤ ተሰማኝና በጣም ደስ አለኝ።

ሌላ ጊዜ ደግሞ በዚሁ ወር የእኛ ቤተ ክርስቲያን ያለችበት አካባቢ አንድ ሰው ያልተመራበት መሬት ስለነበር ለእናቴ "ጸሎት ቤት አካባቢ የነበረውን ነጻ መሬት ተመርቼ ቤትና በረት ብሠራበት እዚያ ብንኖር ለከብቶቻችን በበጋም በክረምትም ይመቻቸዋል።" ብዬ አማከርኳቸው።

እናቴም ወዲያው "አንተን ያስተማረህ እግዚአብሔርና ቤተ ክርስቲያን የት እንደሚልኩህ ሳታውቅ እንዴት መሬት ተመርተህ ቤት ትሠራለህ?" አሉኝ። ይህንንም እኔ ሳላስተውል እግዚአብሔር በእናቴ በኩል ሊናገረኝ የላከው መልዕክት ነው ብዬ ተቀበልኩና አርፌ ተቀመጥኩ። ምክንያቱም በወቅቱ እኔ ሀሳቡን ለእናቴ ሳቀርብ እርሳቸው እንዲስማሙበት እና እንዲመቻቸው አድርጌ ነበር። ነገር ግን ጌታ ቀድሞ ለእናቴ የራሱን ዓላማና ፈቃድ ገለጸላቸውና የኔን ሀሳብ ሳይቀበሉ ቀሩ።

ከዚህ በኋላም እግዚአብሔር ለአገልግሎቱ እንዲለየኝ ቀንና ሌሊት እያለቀስሁ እጸልይ ነበር። ነሐሴ ወር ላይም አንድ ሐሙስ ማታ "ጌታ ሆይ ከዚህ የደም ዕዳ አድነኝ" እያልኩ አጥብቄ እያለቀስሁ ስጸልይ አደርኩ። ጠዋት እንደተለመደው ልጆችና አዋቂዎችን እስከ 5 ሰዓት አስተምሬ ስጨርስ ከብቶቼን ወደ ግጦሽ ወስጄ አሰማራሁ። ከዚያም ወጣ ባለ ጫካ ውስጥ እግዚአብሔር የአገልግሎት አቅጣጫዬን እንዲያሳየኝ ብቻዬን መጸለይ ጀመርኩ። ወዲያውም በዚያው ዕለት አቶ ሱሞሮ የሚባሉ የኛ ክፍለ

ማኅበር ሽማግሌ ወደ እኔ መጡና ከቦቢቾ እኔና አቶ መነሾ ጫሜዕቦ የሚባል ጓደኛዬ በአንድነት በኅዳር ወር (1945 ዓ.ም) የወንጌል መልዕክተኞች ሆነን ወደ ዲላ እንድንሄድ ከከምባታና ሃዲያ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን የተጻፈ ደብዳቤ እንዳመጡ ነገሩኝ። አቶ ሱሞሮ በጊዜው ወደ ቤት መጥተው ሲያጡኝ ከቤት ያለሁበትን የሚጠቁም አንድ ልጅ ይዘው ከብቶቼን እየጠበቅሁ ያለሁበት ሆማንቾ ጫካ ድረስ መጥተው ነበር ደብዳቤውን የሰጡኝ። ደብዳቤውን ስቀበልም ለእኔ ታላቅ ደስታና ሐሴት የማድረጊያ ጊዜ ሆነልኝ። ካስናበትኳቸው በኋላም ወዲያው በአንድ ዛፍ ሥር ተንበርክኬ እግዚአብሔር ጸሎቴን ስለሰማኝና መልስ ስለሰጠኝ በደስታ አብዝቼ አመሰገንኩ።

ወደ ዲላ ለመሄድ በዝግጅት ላይ ሳለሁ በርካታ ፈተናዎች ያጋጥሙኝ ጀመር። በመጀመሪያ የመሄዴን ዜና ከሰማሁ በኋላ ከከብቶቻችን መኃል 11 የሚሆኑ ጥጆች ከተባ ወይም ደስታ የሚባል በሽታ ያዛቸው።

ከዚህ በመቀጠል ደግሞ ፈተናው ከውስጥ ተነሳና የኛ ቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች "ይህንን ሁሉ ንብረት ለማን እና እንዴት ጥለህ ትሄዳለህ?" ብለው መሄዴን ተቃወሙ። ቤት ውስጥም እናቴን እጃቸውን እሾህ ወጋቸውና በጠና ታመሙ። ይሁንና በዚህ ሁሉ ውስጥ እግዚአብሔር ታላቅ የሆነውን የክርስቶስን ፍቅር በልቤ ውስጥ አቀጣጥሎ ነበርና ሁሉንም ወደ ኂላዬ አድርጌ አለፍኩ። መንፈስ ቅዱስ የክርስቶስንና የነፍሳትን ፍቅር በልባችን ካፈሰሰ ከሌሎች ከምንወዳቸው ነገሮች ሁሉ በላይ ስለሚሆን አልፈን ወደ ፊት እንሄዳለን።

እግዚአብሔር ሁሉንም አሳልፎኝ በመጨረሻ የመሄዴ ነገር በመረጋገጡ በምትልከኝ የዲኒቃ ክፍለ ማኅበር ሽኝት ተደረገልኝ። በሽኝቱ ወቅት በዋራሞ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን በተዘጋጀው ሥነ-ሥርዓት ላይ የክፍለ ማኅበሩ ሽማግሌዎች ለእኔ የማበረታቻና የምክር መልዕክት አቀረቡ። በዚህ ወቅት አቶ ሞሎሮ መሲቦ የተባሉ የክፍለ ማኅበሩ ሽማግሌ በ2ኛ ነገሥት ምዕራፍ 4 ላይ ያለውን የኤልሳዕንና የአገልጋዩን ሁኔታ በማንሳት "የኤልሳዕ አገልጋይ የሞተውን ልጅ ለማስነሳት ሮጦ ሄዶ ልጁ ሳይነሳ ሲቀር ቶሎ ተመለሰ፤ ኤልሳዕ ግን ሄዶ በሞተው ልጅ ላይ ሁለመናውን (መላ አካሉን) አድርጎ ሲጸልይ የሞተው ተነሳ። አንተም በሄድክበት ሁለመናህን ሰጥተህ አገልግል" ብለው ታላቅ ምክር ሰጡኝ። ይህ ምክር ያኔ ዲላ ሄጄም ሆነ ዛሬም ድረስ በሕይወቴ ሁል ጊዜ የምጠቀምበት ለጌታ አገልግሎት ራሴን ሙሉ ለሙሉ እንድሰጥ የሚያሳስበኝና እኔነቴን እንድተው የሚያደርገኝ ጠቃሚ ማበረታቻዬ ነው።

## ዘመቻ ጌዴኦ

ከዚህ ሁሉ በኋላ ወደ ዲላ ኅዳር 5 ልንሄድ ከሁለት ቀን በፊት የትራንስፖርት እና የምግብ ገንዘብ ለመቀበል ቦቢቾ ስሄድ ለምግብና ለትራንስፖርት እንዲሆነኝ 20 ብር

ብቻ ሰጡኝ። እኔም ገንዘቡ አይበቃኝም ብል ገንዘብ ፈላጊ ነው ይሉኛል ብዬ እግዚአብሔር የፈቀደው ይሁን አልኩና የሰጡኝን ተቀብዬ ወደ ቤት ተመለስኩ።

ከዚያም ኅዳር 5 ዓርብ ዕለት የመጀመሪያውን የወንጌል ዘመቻዬን ወደ ጌዴኦ ላደርግ ተነሳሁ። በማለዳ ተነስቼም ወደ አሳባ ቁሊቶ ተንዝኩ። ከዚያም ከአሳባ ሻሸመኔ የሚያደርሰኝን መኪና ተሳፍሬ ለትራንስፖርት 4 ብር ከፍዬ ሄድኩ። ከተሰጠኝ ገንዘብ ላይም 16 ብር ብቻ ቀረኝ። ከሻሸመኔ ደግሞ አለታ ወንዶ ድረስ ለመሄድ የጭነት መኪና ላይ ተሳፈርኩ። የጉዞ ሂሳቡም 7 ብር ነበር። ለጉዞ በጭነት መኪናው ላይ 4 ሰዓት የተሳፈርኩ 10 ሰዓት አለታ ወንዶ ደረስኩ። በዚህ ጊዜ የእኩለ ቀኑ ጠራራ ፀሐይ አቃጥሎኝ ደክሞኜ ከመኪና ወረድኩ። አለታ ወንዶም ሚስተር ብራንት የሚባሉ ሚስዮናዊ መጥተው በራሳቸው መኪና ወደ ዲላ ወሰዱኝ። በወቅቱ የዲላ መንገድ በጣም አስቸጋሪ ስለ ነበር ከምሽቱ አራት ሰዓት ላይ በጣም ደክሞኜ ዲላ ገባን። ዲላ ገብቼ የመጀመሪያውን ሌሊት በጉዞ የዛለ ሰውነቴን በማሳረፍ አሳለፍኩ።

ቅዳሜ በማለዳ እንደተነሳን ገና እህል በአፋችንም ሳይዞር ከአለታ ወንዶ ያመጡኝ ሚ/ር ብራንት "የእናንተን ደመወዝ የሚከፍለው ማን ነው?" ብለው ጠየቁኝ። እኔም "የምን ደመወዝ?" ብዬ ጠየቅኋቸው። በእውነቱ የራሴን ኑሮ በተመቻቸ ሁኔታ ወተት፣ ቅቤ እና አይብ እያማረጥኩ ከምኖርበት ለወንጌል አገልግሎት ስወጣ ቤተ ክርስቲያን ቢያንስ ለምንመገበው እና ለምንኖርበት የሚሆን ደመወዝ ትሰጣለች ብዬ ብጠብቅም ሁኔታው ግን እንደዚያ አልነበረም። ቀጥዬም "እኛ ስለ ደመወዝ ከማንም ጋር አልተነጋገርንም፤ ነገር ግን የአገልግሎታችን ባለቤት ሁሉን ያውቃል።" አልኳቸው።

በዚሁ ዕለት ጠዋት ሚ/ር ብራንት ጎላ ወደምትባል ቤተ ክርስቲያን ወሰዱኝ። በጊዜው ጥቂት ወንዶችና ሴቶች ህጻናትን ጨምሮ ተሰብስበው ነበር እና በዚያ ስፍራ በጌዴኦ ምድር የመጀመሪያ የሆነውን መልዕክቴን አቀረብሁ። ስብከቴን በኢሳይያስ ምዕራፍ 53 ላይ በማድረግ ኢሳይያስ ስለ ክርስቶስ አዳኝነት የተነበየው በኢየሱስ ክርስቶስ መፈጸሙን ተናገርኩ። ከዚያም ወዲያው ሐሩሬሳ ወደሚባልና ከዲላ ዝቅ ብሎ የሚገኝ ቦታ ሄድኩ። በዚያ ቦታም ገና የጸሎት ቤት ስላልነበር አቶ ወራሶ ጀልድሶ የሚባሉ ሰው ቤት ነበር አምልኮ የሚደረገው። በዚያ ስፍራም የዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 2 ቁጥር 2 ላይ ያለውን ሀሳብ አንስቼ ኢየሱስ ለዓለም ሕዝብ ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት በሰማይ የሚቆም ጠበቃ እንደሆነ ሰበክሁ።

ከአንድ ሳምንት በኋላም እኔ ከዲላ የ3 ሰዓት ተኩል ያህል የእግር መንገድ ርቀት ላይ የሚገኝ ኔንቃ የሚባል ቦታ ሄጄ እንዳገለግል ወስነው በዚያ ተቀመጥኩ። በጊዜው በጌዴኦ የነበሩ የቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያናት ዘጠኝ ብቻ ስለ ነበሩ እኔ ኔንቃ ስደርስ የተለየ ጸሎት ቤት አልነበረም። የነበሩትም አማኞች 5 ሰዎች ብቻ ነበሩ። እነርሱም፡- አቶ አታራ በቀቱ፣ ሂርቢቾ፣ ጉደና፣ አቶ ዴማ፣ አቶ ሻዕና እና አቶ ኃይሌ ጋንዶ ነበሩ። እኔም አቶ አታራ ቤት እንድኖር ተደረገ። አቶ አታራ በጊዜው ባለሁለት ሚስት

ስለነበር በአንደኛዋ ሚስቱ ቤት ሁለታችን አብረን አደርን እና በሦስተኛው ቀን ወደ ሁለተኛዋ ሚስቱ ቤት ሊሄድ ተነሳ። ይህን ጊዜ እኔ አትሄድም ብዬ ተቃወምኩት። "እኔ አንተ በሌለህበት ባድር ምንም አይፈጠርም። ግን ሌላ የሚመለከት ሰው ግን ክፉ ነገር ይጠረጥራል፤ ስለዚህ መሄድ የለብህም" ስል ሁለቱ ሚስቶቹ ተሳሳቁ እና ሊሄድባት የነበረችው ሁለተኛዋ ሚስቱ «ይህ እንግዳ ባሌን ከለከለኝ" አለች። ያንንም ቀን ከአቶ አታራ ጋር አብረን በአንደኛዋ ሚስቱ ቤት አደርን።

ከዚያም ወዲያውኑ ወደ አቶ ሂርቢቾ እናት ቤት ተዛወርኩ። ለሁለት ዓመት ያህልም በሂርቢቾ እናት ቤት ኖርኩ። የአቶ ሂርቢቾ እናት ወ/ሮ ለሊዩ እንደ ልጃቸው አድርገው ያዩኝና ይወዱኝ ነበር። ቆይቼ ወደ ትውልድ መንደሬ ሄጄ ሚስት አግብቼ ስመለስም ዘመዶቻቸውን ሁሉ ጠርተው ድግስ ደግሰው ለእኔም የመቋቋሚያ ስጦታ 27 ብር ሰብስበው ሰጥተው መልካም አቀባበል አድርገውልኛል። ከእነርሱ ስለይም የሂርቢቾ አባት አቶ ጉደና ካሉበት ቦታ መጥተው አማኞችን ሁሉ ሰብስበው "ይህ ልጅ ብቻውን መሄድ የለበትም፤ በኋላ ብቻውን ሄዶ አንድ ነገር ቢደርስበት ለእኔ ጥሩ አይደለም።" ብለው አስጠንቅቀው ለመጀመሪያ ሚስታቸው ለወ/ሮ ለሊዮ (እኔን ለሚያኖሩኝ) ገንዘብ ሰጥተዋቸው ወደ ነበሩበት አብዮት ወደ (ወደ ሁለተኛ ሚስታቸው) ቤት ተመለሱ። ይህ ሁሉ መልካም የሆነልኝ እንግዲህ ከእግዚአብሔር ምሪትና መልካም ጥበቃ የተነሳ ነው።

በኔንቃ ስኖር የነበረኝ የአገልግሎት ቆይታ ይህን ይመስል ነበር። አገልግሎቱን የጀመርኩት ጠዋት ጠዋት የአካባቢውን ልጆች እየሰበሰብኩ ፊደል፣ ንባብ፣ ጽሕፈት እና የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ በማስተማር ነው። ይህንን ማድረግ ያስቀደምኩበት ዋናው ምክንያት አንደኛ ልጆችን በአካባቢው ከተንሰራፋው እና ከወላጆቻቸው የባዕድ አምልኮ ስርዓት ለመለየት ነበር። በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ በልጆች አማካኝነት ወደ ወላጆች ወንጌልን ለማድረስ ሲሆን ሦስተኛው ምክንያቱ አዲስና የተማረ የጌዴኦ ትውልድ ለማፍራት ነበር። በተጨማሪም ለወደፊት የጌዴኦ ቤተ ክርስቲያንን የሚረከቡ መሪዎችን ለማዘጋጀት ያደረግሁት ይህ የመጀመሪያ ጥረቴ በወቅቱ በጣም ስኬታማ ሆኗል።

ከዚህ በመቀጠልም ወደ ገበያ በመሄድ ገበያ ውስጥ እና ወደ ገበያ በመሄጃ መንገዶች ላይ፤ መንደር ውስጥም እየገባሁ ለሰዎች ወንጌልን እሰብክ ነበር። አንዳንድ ጊዜ ደግሞ የጌዴኦ ሕዝብ በባህሉ የሚሰባሰብበት ሸንጐ አለው፤ በዚያ ሸንጎ ላይ ሰዎች ገበጣ ይጫወታሉ። እኔም ገበጣ በደንብ መጫወት ስለምችል አብሬ ስጫወት እቆይና በመጨረሻ ወንጌልን እሰብካለሁ። እንዲሁም ደግሞ ሰዎች በጋራ በሚሠሩበት ቦታ አብሬ ስሠራ እቆይና ከሥራ በኋላ ወንጌልን እሰብካቸዋለሁ። በዚህ ዓይነት በ1943 ዓ.ም በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት የሐዋርያት ሥራን ስንማር ሐዋርያቱ ወንጌልን በገበያና በሕዝብ መሰብሰቢያዎች እንደሰበኩ የተማርኩትን ተግባራዊ አደርግ ነበር።

አንድ ቀን ከለቻ በሚባል ገበያ ውስጥ ለገበያተኛው ሕዝብ ወንጌል እሰብክ ነበር። ሰዓቱ ከቀኑ 7.30 አካባቢ ነው። ብዙ ሰዎች ተሰብስበው እየሰሙ እያለ ሁለት ወጣቶች ረብሻ አስነስተው ሕዝቡ እንዲበተን አደረጉ። ከዚያም ትልልቅ ዱላ ይዘው እኔን ሊደበድቡኝ ሲሉ ሸሽቼ መሮጥ ጀመርኩ። በነበርንበት ገበያ አቅራቢያ ሐፌሮ የሚባል ተራራ አለ። እኔም ወደዚያ ተራራ በዳገታማው መንገድ ቢያባርሩኝም እየሮጥሁ ሳይዙኝ ማምለጥ ቻልኩ። ሸሽቼ አምልጬ ከተረፍኩ በኋላ ገበያው ውስጥ የሆነውን ስሰማ በተፈጠረው ረብሻ ምክንያት እና ሰዉ ገበያ ላይ መጠጥ እየጠጣ ይሰክር ስለነበር የሰከረው ሕዝብ እርስ በእርሱ ሲደባደብ ሰባት ሰዎች ሞቱ። እኔም ሸሽቼ በማምለጤ ተረፍኩኝ እንጂ ተይዤ ቢሆን ኖሮ ከባድ ድብደባ ሊደርስብኝና ምናልባትም ከሟቾቹ አንዱ ልሆን እችል ነበር። በእርግጥ ጌታችን ስለ ወንጌል መከራ ሲደርስብን ቆመን እንድንሞት አላዘዘንም፤ ይልቁንም ከሐዋርያቱ ታሪክ ከክፉ ሸሽቶ ማምለጥ እንደሚገባ የተማርኩትን በመፈጸም ጌታ አቅም ሰጠኝና ሸሽቼ ማምለጥ ቻልኩ።

በጊዜው የነበረኝ የወንጌል ስብከት እና የማስተማር አገልግሎት በነበርኩበት አካባቢ ብቻ የተገደበ አልነበረም። ከኤንቃ በእግር ጉዞ 40 ደቂቃ ያህል የሚወስድ ቱንትቻ በተባለ አካባቢም አንድ አቶ ዋጃ የሚባሉ ትልቅ ሽማግሌ አማኝ ስለነበሩ ወደዚያ እየሄድኩ እሰብክና አስተምር ነበር።

በአንድ ወቅት ቱንትቻ እየሄድኩ ሳስተምር እንዲህ ሆነ፡- እኔ እያስተማርኩ በነበረው ትምህርት ሌጌ ዋጃ የሚባል የአቶ ዋጃ ልጅ በክርስቶስ አመነ። በዚህ ጊዜ አቶ ሌጌ ሁለት ሚስት ስለነበረው እርሱና ሁለተኛ ሚስቱ ሲያምኑ የመጀመሪያ ሚስቱና ከእርሷ የተወለዱት ልጆች ግን በጣም ተቆጡ። አንድ ቀን ማረሚ የሚባለው የአቶ ሌጌ ልጅ አባቱ በክርስቶስ በማመናቸው ተበሳጭቶ ኃይለኛ የስድብ ቃል በአባቱ ላይ ይናገር ጀመር። ማረሚ ይህን በሚናገርበት ወቅት ምናልባት የ8 ዓመት ልጅ ነበር። አቶ ሌጌ በልጁ ስድብ ተበሳጭቶ በቁጣ ሲነሳ እኔ "ተወው እርሱ ሳይሆን ሰይጣን ነው በእርሱ ላይ አድሮ የሚናገረው" ስለው እርሱም ምክሬን ሰምቶ ስድቡን ታግሶ አሳለፈ። ይህ በሆነበት ማታ እኛ አቶ ዋጀ ቤት አድረን እያለ ገና ሰማይና ምድር ሳይላቀቅ በማለዳ የአቶ ሌጌ ልጅ መምሩ እና ማረሚ እኛ ያደርንበትን ቤት በር አንኳኩ፤ በሩ ሲከፈት ምንም መናገር አልቻሉም። ለካስ የዚያኑ ዕለት ማታ ላይ የአቶ ሌጌ የመጀመሪያ ሚስት እና አራት ልጆቻቸው ሁሉም መናገር የማይችሉ ዱዳዎች ሆነው አድረው ኖሯል። እኛም በፍጥነት ቤታቸው ሄደን ለሁሉም ጸለይንላቸው። ሁሉም በክርስቶስ አመኑ እና የታሰረው አፋቸው ተከፍቶ ወዲያው መናገር ቻሉ። እናታቸው ብቻ ለብዙ ጊዜ ኮልታፋ ሆነው እየተኮላተፉ ይናገሩ ነበር። ዛሬ ማረሚና መምሩ የሚባሉት ሁለቱ የሌጌ ልጆች ወንጌላውያን ናቸው።

አቶ ሌጌ በእምነቱ እየበሰለ ሲሄድም ከሁለቱ ሚስቶቹ አንዷን ፈትቶ እንዲጠመቅ እና ከመጀመሪያ ሚስቱ ጋር ቢጠመቅ መልካም መሆኑን ምክር ሰጠሁት። እርሱም ተስማምቶ መጀመሪያ ሚስቱ የነበረችው የነ መምሩ እናት ነበረችና ከእርሷ ጋር

ለመጠመቅ ወሰነ። ይህቺ ሴት አስቀድማ በጣም ኃይለኛ እና አብሮ ለመኖር አስቸጋሪ የነበረች ብትሆንም እግዚአብሔር ባህርይዋን ፈጽሞ ለውጦ እስከ ዛሬ ድረስ ከአቶ ሌጌ ዋጆ ጋር አብረው በሰላም ይኖራሉ። ሁለተኛይቱ ሚስትም ከአቶ ሌጌ ጋር ከተለያየች በኋላ የወለደችው ተስፋዬ የሚባል አንድ ልጅ ብቻ ስለነበራት ሌላ ባል አግብታ ሠላማዊ ኑሮዋን ቀጠለች።

በዚህ መልኩ አገልግሎቱ ፍሬያማ ስለሆነ የኔንቃው አገልግሎቱም እንዳይበደል ኔንቃ እያደርኩ ሳገለግል እቆይ እና በተወሰነ ቀን ወደ ቱንቲቻ እየመጣሁ በማደር በማለዳ ተነስቼ አገልግሎቱን እሰጣለሁ። አንድ ጊዜ እንደተለመደው ቱንቲቻ አድሬ ከረፋዱ 5 ሰዓት አካባቢ በአቶ ዋጆ ደጅ ለተሰበሰቡ ሰዎች የደህንነት መልዕክት እያቀረብኩ እያለ በድንገት አንዲት ሽጌ የምትባልና ለአራት ዓመት ያህል እብዳ ባሏን፣ ልጆቿንና ቤቷን ትታ በየወንዙ እና በየገደሉ ስትኖር የነበረች ሴት እኔ ወደማስተምርበት ስፍራ መጥታ ቁጭ አለች። በጊዜው ሴትየዋ አይኗ ቀልቶ የእሳት ነበልባል ይመስል የነበረ ሲሆን ጸጉሯም ተንጨፍርሮ የደረቀ ሣር መስሏል። እኔም እያስተማርኩ ሳለ በልቤ "በሐዋርያት ጊዜ ድንቅና ተዓምራት የሠራህ አምላክ አሁንም ተዓምር ለማድረግ ትችላለህና ለክብርህ ስትል በዚህ ስፍራ ድንቅ ነገር እንድታደርግ እለምንሃለሁ" ብዬ ጸለይኩ። ከዚያም ሴትየዋን ተነሺ እና ለአንቺ ሲል ሞቶ የተነሳውን ኢየሱስ ክርስቶስን እመኚ አልኳት። እርሷም እንደታዘዘችው ተነስታ በክርስቶስ አመነች። ወዲያውም ያሠራት ሰይጣን ከእርሷ ወጥቶ ወደ ልቧ ተመለሰች። እኛም እግዚአብሔርን አመሰገንን።

ከሽጌ መፈወስ በኋላም ብዙዎች እየመጡ ከሕመማቸው ይፈወሱና ከሰይጣን እሥራት ነጻ ይወጡ ነበር። ብዙ ቃልቻዎችም በክርስቶስ እያመኑ ከሰይጣን እስራት ነጻ ወጥተዋል። ከዚህም የተነሳ በኔንቃም ሆነ በቱንቲቻ ብዙ ሰዎች በክርስቶስ አምነው በመዳናቸው ወንጌል እየተስፋፋ ሄደ። አንዳንዶች እንደውም ከሌላ ቦታ ሁሉ እየመጡ ያምኑ ነበር። ለምሳሌ አንድ ቃልቻ ሀፈሮ ከሚባል ቦታ ቱንቲቻ ድረስ ከቤተሰቡና ከተከታዮቹ ጋር መጥቶ አመነ።

ይህም ወንጌል በየአካባቢው እየተስፋፋና እያደገ መምጣቱን የሚያሳይ ነበር። እንዳልኩትም በወንጌል የተደረሱ አካባቢዎች ስለበዙ አስቀድመን በሁለት ዙር የሄድነው አራት ወንጌላውያን ሁሉንም ማገልገል አዳጋች እየሆነ ስለመጣ ተጨማሪ ወንጌላውያን እንዲላኩ የሚጠይቅ ደብዳቤ ወደ ከምባታና ሃዲያ ቤተ ክርስቲያን ተጻፈ። ለጥያቄውም ቤተ ክርስቲያናችን ቶሎ ምላሽ ሰጠችና በሦስተኛ ዙር 12 ወንጌላውያን ተጨመሩልን። እነርሱም አቶ ሳህሌ ጆፌ፣ አቶ ኢዩኤል ፋጌ፣ አቶ በቀለ ዋራቶ፣ አቶ ታፈሰ ኢሊጎ፣ አቶ ዳና ዳለሎ፣ አቶ አርፍጮ፣ አቶ ያዕቆብ ባፋ፣ አቶ አብሮ ሐሲሶ፣ አቶ ዘኬዎስ፣ አቶ ፊታሞ፣ አቶ ሱጌቦ፣ አቶ ሰሙሮና አቶ ኤርዱሎ ነበሩ። ከዚያም 16 ሆነን በተለያዩ 16 ቦታዎች ላይ ተመድበን ማገልገላችንን ቀጠልን። እግዚአብሔርም ከእኛ ጋር ሆኖ አገልግሎታችንን በድንቅና በተዓምራቶች እያጀበ

ፍሬያማ መሆን ቻልን። በዚህ ሁሉ የአገልግሎት ቆይታችንም ሚሲዮናዊው ሚስተር ብራንት በታላቅ የአገልግሎት ፍቅር አብረውን አገልግሎቱን ያስተባብሩ ነበር።

እዚህ ጋ ወደ ጌዴኦ ሄደን አገልግሎት እንደጀመርን አካባቢ ከሚስተር ብራንት የቀሰምኩትን ትምህርት ልጥቀስ፡- ጌዴኦ በደረስንበት ወቅት አገልግሎቱን የሚያስተባብሩት በጌዴኦ የሚሲዮናውያን እና የአገሬው ቀደምት አማኞች ነበሩ። እኛ ደግሞ አስር ሆነን መጥተን ሦስተኛ ቡድን ሆንን። በአገልግሎት ሂደትም ሚሲዮናውያኑ በአንድ ጉዳይ ላይ ይወስኑ እና ሁላችን ወደ ምንሰበሰብበት መጥተው ይነግሩናል። የጌዴኦ ቤተ ክርስቲያን መሪዎችም እንዲሁ በራሳቸው ይወስኑና ይነግሩን ነበር። እኔም ይህ አሰራር ችግር ሊፈጥር እንደሚችል ስለገባኝ በየቡድናችን በአገልግሎት ጉዳይ ላይ ወስነን መምጣት እንደሌለብን እና ሃሳቡን አስበንበት መጥተን ውሳኔው በጋራ በተሰበሰብንበት እንዲሆን ጠይቄ በመጨረሻም ሁሉም ተስማሙ።

በዚሁ ጊዜ ሚ/ር ብራንት አጠቃላይ አገልግሎቱን ስለሚያስተባብሩ በትጋት ይሠሩ ነበር። አንድ ቀን ግን ከላከችን የከምባታና ሃዲያ አውራጃ ቤተ ክርስቲያን የሚላከው የቀለብ ገንዘብ ዘገየ። በወቅቱ እኔ ምድቤ ዲላ ስለነበር እዚያው ነበርኩ። ሌሎቹ አገልጋዮች ግን ከያሉበት ገንዘቡን ሊጠይቁ መጡ። ይህን ያዩት ሚ/ር ብራንትም የእሁድ አምልኮ ላይ እየሰበኩ እያለ "የከምባታ እና ሃዲያ አገልጋዮች ለገንዘብ ብላችሁ አገልግሎት አቁማችኋል።" ብለው በጉባኤ ፊት ወቀሱን። እኔም ይህን ስሰማ በመጀመሪያ ገንዘብ ሊጠይቁ በመጡት አገልጋዮች ድርጊት ባልስማማም የሚ/ር ብራንት በቤተ ክርስቲያን አማኞች ፊት ያቀረቡት ወቀሳ ግን ቅር አሰኘኝ። ስለሆነም በዚህ መልኩ አገልግሎት መቀጠል እንደሌለብኝ ስለተሰማኝ ከዚህ በኋላ አገልግሎት መቀጠል የለብንም ብዬ ወቀሳ ለቀረበባቸው የአገልግሎት አጋሮቼ እና ለሚስተር ብራንት "አገልግሎቱን አቁሜ እመለሳለሁ።" አልኩኝ። ሚ/ር ብራንትም እኔ ምድቤ እዛው ዲላ ስለነበር "አንተን አይመለከትህም እኮ" ቢሉኝም እኔ "የከምባታና ሃዲያ አገልጋዮች ስለተባለ ዞሮ ዞሮ እኔም ከዚያው ስለሆንኩ ይህን የሰማ ሰው እንዴት የኔን አገልግሎት ይቀበላል?" ብዬ ተቃወምኳቸው። ሚ/ር ብራንትም በነገሩ ተጸጽተው በሳምንቱ የእሁድ አምልኮ ፕሮግራም ላይ በጉባኤ ፊት ዝቅ ብለው "ባለፈው ሳምንት የተናገርኩት የተሳሳተ ነገር ነው።" ብለው እኛን ይቅርታ ጠየቁ። እኔም ከእርሳቸው ትልቅ ትምህርት ተማርኩ።

ጌዴኦ ሄደን ባገለገልንበት ወቅት በጌዲኦ የነበረንን አገልግሎት ውጤታማ ያደረገው ወቅቱ ለወንጌል ስርጭት ምቹ የነበረ መሆኑ ነው። እኛ ጌዲኦ አገልግሎት በጀመርንበት ወቅት የጌዲኦ ሕዝብ ልብ ልክ ምንም እንዳልተጻፈበት ባዶ ነጭ ወረቀት ነበር። ስለዚህም ምንም ነገር ቢመጣ ለመቀበል ፈቃደኛ ነበሩ። አስቀድመው እንደሌላው የአገራችን ክፍል በአዋጅና በትእዛዝ የኦርቶዶክስ ክርስትናን ተቀብለው የነበረ ቢሆንም ስለ እምነቱ አንገታቸው ላይ ከሚታሰረው ክር ባለፈ የሚያውቁት ነገር አልነበረም። እስልምናም ገና በአካባቢው መምጣት መጀመሩ ነበር። ስለሆነም እኛ በነጣው የወንጌል አዝመራ ላይ መጥተን ዘራን። ሚ/ር ብራንትም ሁልጊዜ "ኬዳሞ

በጌዴኦ ሕዝብ ልብ ውስጥ የሌላ ሃይማኖት ትምህርት ሳይገባ ወንጌሉን ቶሎ እንዝራ። ለዚህ ሕዝብ ወንጌል የመስሚያ ጊዜው አሁን ነው" ይሉኝ ነበር። ይህ አቋም ትክክለኛና እውነት ነበር። እግዚአብሔር በጌዴኦ እንድናገለግለው የሰጠን ዘመን አላፊ በመሆኑና ጊዜው ቆሞ ስለማይጠብቀን በጊዜያችን አገለገልን። ዛሬም አገልጋዮች የሆንን ሁሉ ጌታን ለማገልገል ያገኘነውን ትክክለኛ ዘመን በአግባቡ መጠቀም አለብን።

እኛ ጊዜያችንን ፈጽሞ ለሌላ ነገር ሳናውል ወንጌልን እንሰብክ ስለነበር በጥቂት ዓመታት አገልግሎታችን በእግዚአብሔር ኃይል እና በመንፈስ ቅዱስ መሪነት በጌዴኦ ምድር ወንጌል ተስፋፍቶ ጠንካራ ቤተ ክርስቲያን ተመሰረተች። በጊዜው ወንጌልን መስበክ ብቻ ሳይሆን ያመኑትን በማስተማር ማሳደግና ለአገልግሎት ማዘጋጀትም ሌላው ዋና አገልግሎታችን ነበር። ስለዚህም በአብዛኛው ማታ ማታ በኩራዝ ብርሃን መጽሐፍ ቅዱስ እናስተምር ነበር። ይህ ፍሬያማ ስለነበርም ነው እኛ ጌዴኦን ለቀን ስንወጣ ያስተማርናቸው አማኞች ወዲያውኑ የኛን ቦታ ተክተው ወንጌል መስበክ እና ቤተ ክርስቲያን መምራት የጀመሩት። እኛ ከተመለስን በኋላም ከከምባታና ሃዲያ ሌሎች ወንጌላውያን ወደዚያ ስፍራ አልሄዱም።

በጌዴኦ የወንጌል ብርሃን ሲበራ የመጣው ልዩነት እና ወንጌል እንዴት እየተስፋፋ እንደነበር የሚያሳይ አንድ ታሪክ አለ። እኛ ወደ ጌዴኦ ከመሄዳችንና ወንጌል ከመስበኩ በፊት እዚያ ይኖር የነበረ አንድ አቶ ሂርቢቾ ጉዳና የሚባል ሰው ነበር። ይህ ሰው ሁል ጊዜ የሚወልዳቸውን ልጆች ሰይጣን ይገድልበት ስለነበር ከሰይጣን ለመሸሽ ከሚኖርበት ኄንቃ ተነስቶ ኡራጋይ ወይም ላዮ ወደሚባል አካባቢ ሄደ። ሆኖም ሰይጣን ወደዚያ ከሄደ በኋላ የተወለዱትንም አልማረለትም። በዚህ ዓይነት ግራ የሚያጋባና ተስፋ አስቆራጭ ሁኔታ ውስጥ እያለም በጌዴኦ አዲስ እምነት እንደገባና ሰዎች በክርስቶስ ኢየሱስ በማመን ከሰይጣን ባርነት ነጻ እየወጡ እንደሆነ ሰማ። እርሱም ይህን ሲሰማ ወደ ጌዲኦ ተመልሶ ጌታን በማመኑ የሚወለዱለት ልጆች ሞትም ቀረ።

አንድ ሰውም እንዲሁ ያ ሰውዬ ሄዶ ከነበረበት ላዮ አካባቢ መጣና ወንጌል መሰከርኩለት። እርሱም "ወደ ላዮ ኑ እኔም ቤተሰቤም እናምናለን" አለ። እኔም ከእርሱ ጋር ቀጠሮ ያዝኩ እና በቀጠሮአችን ቀን ከአቶ ኃይሌ እና አቶ ሂርቢቾ ጋር ሆነን ካለንበት ኄንቃ ወደ ላዮ ሄድን። ከእኛ ጋር ቀጠሮ የያዘውን አቶ አርቢ የሚባል ሰው አገኘንና እርሱ ሚስቱና አቶ አበዩ የሚባል ልጁ ሆነው ክርስቶስን አመኑ። በዚህ ጊዜ ሕዝብ ተሰብስቦ ሲንጫጫ አየንና ምክንያቱን ስንጠይቅ የአካባቢው ባላባትና ነዋሪው ለመንግስት ግብር ሊሰጡ በተሰበሰቡ እንስሳት (በግ፣ በሬና የፍየል ሙክት) ጉዳይና በሌሎች ልዩ ልዩ ነገሮች ዙሪያ ይነጋገሩ ነበር። በጊዜው በነበረው ልማድ መሠረት አንድ ባላባት እና የአካባቢው ሕዝብ ተሰብስቦ ሕዝቡ ለየትኛው ንብረት ምን ዓይነት ግብር መስጠት እንዳለባቸው ይነጋገሩ ነበር። በጊዜው ግብር መሰጠቱን የሚመዘግብላቸው ጸሐፊ የሚሆን ሰው አጥተው ተቸግረው ነበር። በኋላም እኔን ጠየቁኝ እና ልጽፍላቸው ተስማማሁ። በጊዜው በአንድ ሰነድ 3 ብር ይከፈል ስለነበር

ባላባቱም ይህንኑ እንዲከፍሉ አዝዞ 8 ያህል ሰነድ ጻፍኩላቸው። ከዚያም ገንዘብ ሊከፍሉኝ ሲሉ እኔ እግዚአብሔር ማስተዋል ሰጠኝ እና "ከገንዘብ ይልቅ እኔ እራሴ የምሰጣችሁ ስጦታ አለኝ አልኳቸው። ከፈቀዳችሁልኝ የመጣሁበትን ዓላማ ልንገራችሁ ስላቸው እነሱም ፈቃደኛ ሆኑ። ከዚያም በመካከላቸው ቆሜ ከሮሜ ምዕራፍ 1 ከቁጥር 16-32 ያለውን አንብቤ የደህንነት መልዕክት ሰበክሁ። ክርስቶስን ማመን ለሚፈልጉም ጥሪ አቀረብኩ። አራት ሰዎች ተነስተው አመኑ። ባላአባቱም ተነስቶ እኔ ስለዚህ ነገር ይርጋ ዓለም (በጊዜው የጠቅላይ ግዛቱ ዋና ከተማ በነበረችው) እና ዲላ ሰምቻለሁ። እናንተም ማመን ትችላላችሁ አላቸው። እኔም ይህንን መልካም ዕድል መጠቀም ስለነበረብኝ ልጆቻችሁን ከሰጣችሁኝ አስተምርላችኋለሁ ብዬ ፈቃዳቸውን ጠየቅሁ። እነርሱም ፈቃደኛ ሆኑና በማግስቱ ብዙ ልጆች ተልከው ሊማሩ መጡ። እኔም በትልልቅ የዝግባ ዛፎች ሥር ልጆቹን አስቀምጬ ማስተማር ጀመርኩ። ጠዋት ጠዋት ከ2-5 ሰዓት ባለው ጊዜ ልጆቹን ሳስተምርም ቆየሁ።

በዚያን ዕለት ካመኑት ሰዎች መካከል አቶ ዱቤ ቲንማዬ የተባሉ ሰው እና ባለቤታቸው ይገኙበታል። ከዚያም በኋላ በርካታ ሰዎች አምነዋል። ያኔ ማመን ትችላላችሁ ያለው ባላባትም አቶ ብሬ ቡሽ የሚባል ሰው ነበር። በዚህ ዓይነት ፍሬያማ የሆነ ሥራ ለ15 ቀናት ያህል ስንሠራ ቆይተን የአንድ ቀን መንገድ ስለነበር ከምሽቱ 11 ሰዓት ላይ ከላዮ ተነስተን በ12 ሰዓት ዲላ ደረስን።

በዚህ ጉዞ ወቅት እኔ በድንገት እግሬን አመመኝና ምሽቱን እዚያው አከመውኝ ሦስት ያህል መርፌ ተወግቼ በወቅቱ ቢሻለኝም ያ ሕመም ዛሬ ድረስ አልፎ አልፎ እየተነሳብኝ መጠነኛ ሕመም ይሰማኛል። ይሁንና  ከአንድ ወር በኋላ ወደ ላዮ ለመመለስ እቅድ ይዤ ስለነበር ሌላ አገልጋይ ጨምሬ ተመልሼ ሄድኩ። ተመልሰን በሄድን ጊዜም ለካስ ከዚህ በፊት በነበረን አገልግሎት ደስ ያልተሰኙ የአገሩ የመሬት መልከኞች አድማ አድርገው ወታደሮች አዘጋጅተው ጠብቀውን ኖሯል። እኛም እንደሄድን በቀጠሯችን መሠረት የተሰባሰቡትን ልጆች አስተምረን ከበፊቱ ባላባት ጋር እያወራን ሳለ ወታደሮች መጥተው "ማንን አስፈቅዳችሁ ነው የምታስተምሩት?" ብለው ጠየቁን። እኔም ወዲያው "እናንተስ እኔን የምትጠይቁበት ምን ሥልጣን ተሰጥቷችኋል" ስል መልሼ ጠየቅኋቸው። እነርሱም ፈቃድ አለን ብለው ከጠቅላይ ግዛት የተሰጣቸውን አንድ ወረቀት አሳዩኝ። እኔም ወረቀቱን ተቀብዬ አንበብኩና "ይህ ፈቃድ የተሰጣችሁ ወስላታ (ወንጀለኛ) እንድትይዙበት ነው። እኔ ወስላታ አይደለሁም። ባላባቱና ሕዝቡ አውቀውኝና ተቀብለውኝ ልጆቻቸውን እያስተማርኩ ወንጌል እሰብካለሁ።" ብዬ ስመልስላቸው "ታዲያ ወንጌል የምትሰብከው በማን ፈቃድ ነው?" አሉኝ። በዚህ ጊዜ የማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 28፡ 18-20 ያለውን መጽሐፍ ቅዱሴን ገልጬ አንብቤ በሰማይና በምድር ሥልጣን ያለው ጌታ ወደ ዓለም ሁሉ እየሄድን ወንጌልን እንድንሰብክ አዝዞናል አልኳቸው። በዚህ ጊዜ የሚሉትን ያጡት ወታደሮች አራት ስለነበሩ ደብድበው ሊወስዱኝ ይችሉ የነበረ ቢሆንም ሕዝቡ እኛን ስለሚያግፈን ያንን ማድረግ አልቻሉም። በዚህ ዓይነት ስንሟገት እስከ ማታ ቆየንና

ጠዋት በ2.30 ሰዓት ላይ ለመገናኘት ቀጠሮ ይዘን ተለያየን። እኛ ወደ ስፍራው ስንደርስ ግን እነርሱ ሳይመጡ ስለቀሩ አገልግሎታችንን ቀጠልን።

በላዮ የነበረን አገልግሎት ውጤታማ እንደሚሆን እግዚአብሔር ሊያሳየን በመሻቱ ገና ለመጀመሪያ ጊዜ ስንመጣ የተፈጸመ አንድ አጋጣሚ ነበር። ነገሩ የተፈጸመው ለመጀመሪያ ጊዜ ላዮ በመጣንበት ቀን ምሽት ላይ ነበር። በዚያ ዕለት ማታ ከምሽቱ አራት ሰዓት አካባቢ እኛ በእንግድነት በገባንበት ቤት ለማደር ተኝተን እያለ አንድ ሰዉ እየጮኸ ወዳለንበት መጣ። በኋላ ስንሰማ ሰውዬው ጅብቾ የሚባል ለሰባት ዓመታት ያህል ሕመምተኛ ሆኖ ከቤተሰቡ ተለይቶ የአገሩ ሰዎች በባእድ አምልኮ ሥርዓታቸው መሠረት በዓመት ሁለት ጊዜ በሬ፣ በግና ፍየል እየያዙ ሄደው ለመስዋዕት እያረዱ በሚሰግዱበት እባብና ዘንዶ በሞላበት ሐይቅ ዳርቻ ይኖር ነበር። እኛ የመጣን ዕለትም ምን እንዳመጣው ሳናውቅ ያለንበት መጥቶ ሲጮህ ከተኛንበት ተነስተን አገኘነውና በክርስቶስ እንዲያምን ወንጌልን መሰከርንለት። ካመነ በኋላም ስንጸልይለት በበሽታ ያሰቃየው የነበረው ለሰባት ዓመታት ያሰረው አጋንንት ጥሎት ሄደና ተፈወሰ። እኛም በርበሬ ይመስል ከነበረ ዓይኑ ጋር እንደጫካ ተንጨባሮ ያስፈራ የነበረ ፀጉሩን አስተካክለን ወደ ቤተሰቦቹ ልከን አስጠራናቸውና ተያይዘን ወደ መኖሪያው አካባቢ ሄድን። ከዚያም ባዩት ነገር ተደንቀው ቤተሰቡም የአካባቢው ሰዎችም ክርስቶስን አመኑ።

ከዚህ ታሪክ መፈጸም በኋላ ከላይ የጠቀስኳቸው በርካታ ድሎችን እግዚአብሔር በዚህ አካባቢ ሰጠን። ከዚህም የተነሳ ጸሎት ቤት ለመሥራት አማኞችን አስተባብረን ተሠራ። ነገር ግን ብዙም ሳይቆይ ከፍ ያለ ተቃውሞ ተነስቶ ትርምስ በመፈጠሩ ጸሎት ቤቱን ተቃዋሚዎች አፈረሱት። ብዙ ክፉ ነገሮችና አሁን ለማንሳት የማልፈልጋቸው እርሞች በዚያ ዕለት ተሠሩ። በወቅቱ እኛ በጣም አዝነን የነበረ ቢሆንም ዛሬ ያ ሁሉ አልፎ በላዮ ቤተ ክርስቲያን አሁንም አለች። ክብር ለእግዚአብሔር ይሁን!!

በቋሚነት በምኖርበት በቱንቲቻም እንዲሁ ብዙ ፍሬ ያስገኙ አገልግሎቶች ነበሩኝ። እንደተለመደው ወንጌልን በልዩ ልዩ ቦታዎችና አጋጣሚዎች እየሰበክሁ ልጆችን እና አዋቂዎችን ለየብቻ እያደረግሁ ፊደል፣ ንባብና ጽሕፈት አስተምራለሁ። የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርትም የእስራኤልን ታሪክ እና ሌሎች ታሪኮችን አስተምር ነበር። እግዚአብሔር ረድቶንም በኔንቃ እንደሆነው ሁሉ ቱንትቻም በየእሁዱ ካመኑ ሰባት ሰዎች መባ፣ አሥራት እና ስጦታ ሰብስበን የጸሎት ቤት መሥራት ችለናል። ይህ ውጤታማ ሊሆን የቻለው እኛ ሰዉን ስጡ እያልን ስናስተምር ራሳችንም እየሰጠን በተግባር እናሳይ ስለነበር ነው።

## ስለ ወንጌል ዋጋ መክፈል

ቱንቲቻ እያለን ወንጌልን ስንሰብክ እና እኔ በዚያ ስፍራ ሆኜ አገለግል በነበረበት ወቅት አስቸጋሪ ሁኔታዎችም ያጋጥመኝ ነበር። ብቻዬን ሳለሁ ፈተናዎች ሲያጋጥሙኝ

ብዙም አይደንቀኝም ነበር። በኋላ ትዳር ይዤ ባለቤቴን ወደ ጌዲኦ ካመጣሁ በኋላ ግን የደረሱት ችግሮች ለኔ አስጨናቂ ነበሩ።

እኔና ባለቤቴ የምንኖርበት ቤት አስተማማኝ የሣር ክዳን ስላልተደረገለት በየቀኑ በእንስት ቅጠል እየከደንን እናድር ነበር። አንድ ቀን ግን በጣም ኃይለኛ ዝናብ ስለጣለ ቤቱን በሙሉ በውሃ አጥለቀለቀው። የምንለብሰው ልብስ፣ የቤት ዕቃዎች፣ የምንበላው ምግብ፣ ዱቄት ሁሉ ሳይቀር አበላሸብን። በዚህ ጊዜ ባለቤቴ ብዙነሽ አኖሴ እና እኔ አዲስ የተወለደው ልጃችን ዳዊትን በመያዝ በላያችን ላይ ሰሌን ደርበን ዝናቡ ሲዘንብ መዝሙር እየዘመርን ነበር። በጊዜው የምንዘምረው መዝሙር በሃዲይኛ "ዋኢንንኔቴ" የሚል ሲሆን ትርጉሙም "እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ነው" የሚል ነበር።

በዚህ ሁኔታ ውስጥ እያለንም አቶ ዋጆ የሚባሉ የአካባቢው ሽማግሌ ወደ እኛ ቤት መጡ እና "ልጆች በነፍስ አላችሁ?" ብለው ጠየቁን። ወደ ቤታችን ሲገቡም ቤቱ ውሃ በውሃ መሆኑን አዩና በጣም አዘኑ። ሆኖም ምንም ሊያደርጉልን ስላልቻሉ ጸልየውልን ወደ ቤታቸው ሄዱ።

በኋላም እኔ ባለቤቴን እንዲህ አልኳት። "እኛ ከዚህ አገር ለቅቀን መሄዳችን አይቀርም፤ ነገር ግን ይህ እኛ ላይ የደረሰ ነገር መቼም ከዚህ ቦታ አይጠፋም። እኛ ብንሞት እንኳን የሚጠፋ ስላልሆነ ለብዙ ትውልድ ፍሬ የሚያፈራ ነው" አልኳት። እርሷም ደስ አላት። በኋላ የቱንቲቻ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን አባላት አንድ ማለዳ የሦስት ሰዓት መንገድ ያህል ወደ ዲላ አካባቢ ሁሉ ሄደው ሌሎች ሴቶችን አስተባብረው በማምጣት በዝማሬና በታላቅ ደስታ ሥራ ሠርተው ቤታችንን በሣር ተከደኑ። በዚህ ጊዜ ሴቶቹን ያስተባበሩት አንዲት ወ/ሮ ጎሎሎ የሚባሉ እናት ነበሩ።

ባለቤቴ ወ/ሮ ብዙነሽ አኖሴ ወደ ዲላ ከመጣች በኋላ የሳንባ በሽታ ተጠቂ ሆና በኃይል ትታመም ነበር። አንድ ቀን እርሷን ለማሳከም ወደ ዲላ ሄደን ስንመለስ መንገዳችን ላይ ከፍ ያለ ዳገት ስለነበር እርሱን እየወጣን እያለ በኃይል አሳላት እና ብዙ ደም አስተፋት። በዚህም በጣም ተዳክመችና መሄድ አቅቶን ቆመን ጸለይን። በኋላም እግዚአብሔር ረድቶን ቀስ እያልን ሄደን ቤታችን ገባን። ዛሬ መለስ ብዬ ሳየው ባለቤቴ የተፋችው ደም በዚያ ቦታ በከንቱ ፈስሶ አልቀረም። ቱንቲቻ ያለችው የቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን እድጋ ሰፍታ በ1995 ዓ.ም የምስጋና ቀን ተዘጋጅቶ ተጋብዤ ወደ ስፍራው በመሄድ ጌታን ማመስገን ችያለሁ።

ቱንቲቻ ሳለሁ የገጠመኝና ከሁሉም አስደናቂ እና የጌታን ጥበቃ ያየሁበት አንድ ገጠመኝም ነበረኝ። በጊዜው ሁል ጊዜ እንደሚደርገው ጠዋት ጠዋት ልጆችን፣ አዋቂ ሴትና ወንዶችን እየሰበሰብኩ አስተምር ነበር። ከማስተምራቸው ሰዎች መካከልም አንድ አቶ መንገሻ ዋጆ የሚባል ሰው ጌታን ሳያምን በፊት ያገባቸው ሁለት ሚስቶች ነበሩት። እኔ በማስተምርበትና የተማሪዎቼን ስም መዝገቤ በምይዝበት ጊዜ አንደኛዋ ሚስቱ ሁል ጊዜ ምንም ነገር ሲያስደነግጣት "መንገሻ" ብላ የባሏን ስም ስለምትጠራ

"ሽጌ መንገሻ" አልኳት። ሌላዋ ደግሞ ስትደነግጥ የምትጠራው "ዱሎ" እያለች የአባትዋን ስም ስለነበር እኔም "ዘነበች ዱሎ" ብዬ እጠራት ነበር። ይህ ነገር ለካስ እኔ ሳላውቅ አቶ መንገሻን አስቀይሞት ቂም ይዞብኛል።

አንድ ቅዳሜ ቀንም ወደ ገበያ ሄዶ ሲመለስ መጠጥ ጠጥቶ ስለሰከረ ሽጉጥ ይዞ ሊገድለኝ ወደ እኔ ቤት መጣ። በጊዜው እኔ ለጸሎት ወደ ዲላ ሄጀ ስለነበር ቤት አልነበርኩም። በዚያ ዕለትም ወደ ቤቴ ልመለስ ተነስቼ የነበረ ቢሆንም ወንጌላዊ በቀለ ወርቁ የሚባል ዲላ አብሮኝ የነበረ አገልጋይ አትሂድ ብሎ መለሰኝ። እኔም "የጌታ ፈቃድ ይሆናል" ብዬ ቀረሁ። አቶ መንገሻ ግን ቤት ያለሁ መስሎት ቤት ገብቶ ሦስት ጥይት በጨለማ ከተኮሰ በኋላ ከውጪ ሆኖ አንድ ጥይት ተኩሶ ወደ ቤቱ ተመለሰ። ከዚያም ነጋዴ ስለነበር ቤቱ ያስቀመጠውን ብር ሰብስቦ ከአገር እጠፋለሁ ብሎ ወጣ። ይህን ጊዜ ባለቤቱ ዘነበች እና ቢጡ የምትባል የጓደኛው ሚስት እንዲመለስ እየለመኑ ተከትለውት ዲላ ደረሱ። እኔም ዲላ አድሬ ወደ ቤቴ ለመመለስ መንገድ ስጀምር ከሴቶቹ ጋር በጠዋት (12:30 አካባቢ ይሆናል) ተገናኘንና "ምን ሆናችሁ?" ብዬ ስጠይቃቸው በዚያ ዘመን የጌዲኦ ሴቶች ውሸት መናገር አያውቁምና ወ/ሮ ዘነበች የሆነውን ሁሉ በዝርዝር ነገሩኝ። እኔም የሆነውን ከሰማሁ በኋላ ዲላ በማደሬ እግዚአብሔር እንዳዳነኝ ስለገባኝ እዚያው ከሴቶቹ ጋር እግዚአብሔርን ስለማዳኑ አመሰገንን። ለእነርሱም "መንገሻን ካገኛችሁት እግዚአብሔር እኔንም አንተንም አድኖናልና ተመለስ" ብሎሃል ብላችሁ ንገሩትና ይምጣ ብያቸው ተለያየን። በኋላም አግኝተው ነገሩት።

እኔ ቤቴ ስደርስ የቤተ ክርስቲያናችን ሰዎች በጠቅላላ እኔ ቤት ተሰብስበው የመንገሻን አባትና ወንድሞች መንገሻን ካለበት አምጡ እያሉ በጣም ሲጨቃጨቁ አገኘኋቸው። እግዚአብሔር በጊዜው ለኔ ማስተዋል እና የልብ ስፋት ስለሰጠኝ ለተሰበሰቡት እግዚአብሔር ሁላችንንም ከክፉ ጥፋት አድኖአልና እግዚአብሔርን አመስግኑ አልኳቸው። ሁላችንም ደስ ተሰኝተን የምስጋና ጸሎት ከጸለይን በኋላ ዕለቱ እሁድ ስለነበረ ለአምልኮ ወደ ጸሎት ቤታችን ገባን። ጸሎት ቤት ውስጥ እኔ እየሰበክሁ እያለም ሁለቱ ሴቶች አቶ መንገሻን ይዘውት መጡ። አቶ መንገሻም ጸሎት ቤቱ ውስጥ ገብቶ ሽጉጡን በአባቱ አቶ ዋጆ እግር ሥር ጥሎ በደረቱ መሬት ላይ ተደፍቶ ተንሰቅስቆ አለቀሰ። ከዚያም እየጮኸ ወደ እኔ መጥቶ እግሬ ሥር ተደፋ። እርቅ ሆነ፤ ሰላም ሰፈነ። ቤተ ክርስቲያናችንም ከዚህ ታሪክ በኋላ እንደገና በደስታ አገልግሎቷን ቀጠለች። እግዚአብሔር ስለሠራው ሁሉ ክብርና ምስጋና ለስሙ ይሁን!!

እዚህ ጋ ታሪኬን ወደ ኋላ መለስ አድርጌ የሕይወት መንገዴ አጣማሪ የሆነችው ባለቤቴን እንዴት እንዳገባኋት እና እንዴት በጌዴኦ አብረን ማገልገል እንደጀመርን ብተርክ መልካም መስሎ ታየኝ። በእርግጥ እንዴት እጮኛ እንደያዝኩ፣ ወደ ጌዴኦም ባለቤቴን ይዤ መጥቼ ማገልገል እንደጀመርኩ ከታሪኩ ቅደም ተከተል አንጻር በትንሹ አውስቻለሁ። ነገር ግን አጠቃላይ የጋብቻ ታሪኬን፣ የኔን የልብ መሻት እና

የእግዚአብሔርን ሥራ እንደሚገባ አልተናገርኩም። በኋላም የምትርክላችሁን ድሎቼን እና ፈተናዎቼን በሚገባ እንድትረዱ ገና ከሻሾን ቀይታዬ እና የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪ እያለሁ ከነበረው ሁኔታ ተመልሼ በመጀመር በሚቀጥለው ምዕራፍ ላይ አጫውታችኋለሁ።

# ምዕራፍ ፲

# ጋብቻ

ኬዳም በጉርምስናው ወቅት መጠጥ የሚጠጣ፣ ጭፈራ እና ጨዋታ የሚያበዛ አልፎ አልፎ ልጃገረዶችን የሚያሸኮረምም እና ማማገጥ የሚወድ፤ ተቆጣጣሪ የሌለው ሞገደኛ ወጣት ነበር። ያኔ የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌልን አምኖ በቀላሉ እጅ እንዳያነሳ ያደረገውም ይሄው የዓለማዊነት ሕይወት ጣፍጦት በቀላሉ መተው ስለተቸገረ ነበር።

አንድ ቀን እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ መንፈሱን አሸንፎት ጌታ ኢየሱስን በልቡ ካነገሰ በኋላ የቀድሞ ክፉ ልምምዶቹ በሙሉ ቀስ በቀስ ከሕይወቱ ተራገፉ። በዚሁ ጊዜ ያለምንም ቀጣይ ዓላማ ከየልጃገረዶቹ ጋር ያደርገው የነበረው ቅርርብም ቆመ። እርሱ እጅ እና እግሩን ለወንጌል አስገዝቶ ተሰብስቦ ሲቀመጥም ለእርሱ በጎ አሳቢ የሆኑ ሰዎች አንዷን ልጃገረድ መርጦ እንዲያገባ ያሳስቡት ጀመር፤ በአንድ በኩል ወላጅ እናቱ ወ/ሮ ሺቢቤ ሸበላው ልጃቸው ቶሎ አግብቶ የልጅ ልጅ እንዲያሳቅፉቸው በማለም በሌላ በኩል ደግሞ የቤተ ክርስቲያን ወንጌላውያንም ቶሎ አግብቶ እንዲያርፍ በማሰብ እንዲያገባ ይወተውቱታል።

ይኸው የሰዎች ጥያቄ እና የራሱም የወደፊት የትዳር አጋርን የማግኘት መሻት በጉዳዩ ላይ እንዲያስብ ያደርጉት ጀመረ። በዚሁ የትዳር ሃሳብ ውስጥ እንዳለም ኬዳም አንድ ነገር ይታዘብ ጀመር።

የኬዳም ታላቅ ወንድም ፈይሳ ያገባት ሚስት ለባሏ መልካም እና የምታስደስት አልነበረችም። በተለይም ፈይሳ እንግዳ ወደ ቤት ይዞ ሲመጣና ጓደኞቹን ሲጋብዝ ባለቤቱ ፈጽሞ በመልካም ሁኔታ ለማስተናገድ ፈቃደኛ አልነበረችም። ፈይሳ ጓደኞቹን ያመጣ እና ቤቱን ከሞላው ወተት እና የሚበላ ነገር እንድታቀርብ ሲፈልግ እርሷ ግን እንግዶቹን በዝምታ መሸኘት ትመርጣች። በዚህ ጊዜ ፈይሳ እንግዶቹን እራሱ የቻለውን ያህል አስተናግዶ ለመሸኘት ይገደዳል። ከዚያም ወደ ቤት ተመልሶ ሚስቱን መደብደብ አምባጓሮ ውስጥ ይገባል። ኬዳም ይህን ሁኔታ በተደጋጋሚ በመታዘቡ ትዳርን ሲያስብ ከባድ ነገር እንደሆነ እንዲሰማው አድርጎታል።

ስለሆነም ስለሚመሰርተው ትዳር እና ስለሚያገባት ሚስት በተደጋጋሚ በእግዚብሔር ፊት እየቀረበ ብዙ ይጸልይ ጀመር። በዚሁ ዓይነት ሁኔታ ውስጥ እያለ አንድ ዕለት ለፈረስ የሚሆን ሣር ለማጨድ ወደ ሜዳ ወርዶ እያለ እንደተለመደው ራሱን ከእግዚአብሔር መንፈስ ጋር እያገናኘ እና በዝማሬ እግዚአብሔርን እያመሰገነ

*አጨዳውን ያካሂድ ጀመር። ኬዳሞ የሻሸን ምድር የተንጣለሉ ሜዳዎች ላይ ከብቶች እያገደ፣ ፈረስ እየጋለበ እና በእግሩ እየተሯሯጠ አድጓል። በዚሁ ወይና ደጋማ የአየር ንብረት ባለው አካባቢ ረግረጋማ ስፍራዎች የሚበቅለውን የሻሸን የጋማ እና ለቀንድ ከብቶች ምግብ የሚሆን ሣር እያጨደም በመንፈሱ የእግዚአብሔርን ታላቅነትና ጌታ በእርሱ ሕይወት የሠራውን ሥራ ያወድስ ነበር።*

*ከቆይታ በኋላም የምስጋና ዝማሬው ተቀይሮ ስለ የቃል ኪዳን ሚስት የሚያወሳ ዝማሬ አስታውሶ መዘመር ጀመረ። ይህን መዝሙር በማስተዋል ሆኖ በተደጋጋሚ ሲዘምረው መዝሙሩ የቃል ኪዳን ሚስቱን ትቶ ሌላዋን የሚያገባ ፍርድን እንደሚቀበል ያውም ሲዖል እስከመድረስ ድረስ ያለ ፍርድን እንደሚቀበል ያትታል። ኬዳሞ በዚህ ጊዜ ታላቅ ወንድሙ ያለውን የትዳር ሕይወት አስታውሶ "እኔም ድንገት አመጸኛ ሚስት ባገባ ከእርሷ ጋር በሰላም  መኖር እንዴት እችላለሁ? እናም እርሷን ፈትቼ ወደ ሲዖል መውረዴ አይደል?' የሚል ኃይለኛ ስጋት ተሰማው። ወዲያውም ሣር አጨዳውን ትቶ እዚያው ያጨደው ሣር ላይ ተንበርክኮ በእምባ የታጀበ የልመና ጸሎት ይጸልይ ጀመር። "እግዚአብሔር ሆይ፦ ካንተ የሆነች አንተን የምትወድ፤ ላንተ የምትገዛ አንተን የምታከብር፤ እኔንም እንግዶችንም አክብራ የምትቀበል ሚስት ስጠኝ' እያለ ጸለየ። በተለይ እንግዶችን ለመቀበል እንደ ወንድሙ ሚስት ክፉ ያልሆነች ሴት እንዲሰጠውም አጥብቆ ጸለየ። ከዚያም ለስለስ ያለ ቀዝቃዛ ንፋስ ፊቱን እየዳሰሰው ውስጡም እግዚአብሔር አንድ ቀን ይህንን ልመናውን እንደሚመልስ እየተሰማው ያጨደውን ሣር ተሸክሞ ወደ ቤቱ አመራ።*

-----------------//-----------------

ከላይ የገለጽኩት ታሪክ የተፈጸመው በ1944 ዓ.ም ሲሆን በጊዜው እኔ በቢቾ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ተማሪ ነበርኩ። ስለ ጋብቻ ከአገልጋዮችም ሆነ ከእናቴ የሚመጣው ጥያቄ በጉዳዩ ላይ እንዳስብ ቢያደርገኝም እኔ ግን ምንም እርምጃ ለመውሰድ አልሞከርኩም። ይልቁንም በታላቅ ጉጉት የጀመርኩትን የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቴን በትጋት እከታተል ነበር። አንድ ቀን ግን ማግባቴን ከሚፈልጉ አገልጋዮች መካከል አንዱ የሆነው ጋሼ ሳህሌ የሚባል ወንጌላዊ ካለችበት መንደር አንዲት እህት ወደ እኔ ላከ።

ወንጌላዊው ያኔ ለኔ ጥሩ ሚስት ልትሆን ትችላለች ብሎ ያሰባት ብዙነሽ አኖሌ የምትባል ከኛው አገር ሆና ከሌላ መንደር የተገኘች ኮረዳ ነበረች። ጋሼ ሳህሌ እኔ ብዙነሽን እንዳገባ ስላሰበም ጉዳዩን ለኔ ነግሮኝ ብዙነሽን የምተዋወቅበትን ሁኔታ አመቻቸ። እናም የዚያን ዕለት ብዙነሽ የተደገሰላትን ሳታውቅ ወደ ቦቢቾ ተላከች። እኔም እርሷን ለመተዋወቅ በጉጉት ጠብቄያት በመጣች ዕለት ግን ጥሩ ልብስ ለብሼ ከመዘጋጀት ይልቅ ቁምጣና ቡልኮ ለብሼ የመጣችበት ቦታ ሄጄ አነጋገርኳት። ማንነቷን፣ ከየትና ለምን እንደመጣች ጠየቅኋት። ከዚያም እርሷ ያለችበት መንደር ድረስ ሄጄ ላያት ወስኜ ቀጠሮ ሰጥቻት ተለያየን።

ትምህርት ቤት ለእረፍት ሲዘጋ በቀጠሮዬ ዕለት ብዙነሽ ወደምትኖርበት መንደር ሄድኩ። እኔ ገና ወደ እርሷ መንደር እየተጓዝኩ እያለም እርሷ ከሰፈሯ ሴቶች ጋር ሆና የጎጆ ቤት ጣራ መክደኛ የሚሆን ሣር ሲያመጡ ወደ ሜዳ ሲሄዱ አገኘኋቸው። በዚህ ጊዜ እኔ በልቤ አንድ ውሳኔ ወሰንኩ። ይህ የእርሷን ማንነት የሚያሳይ ትልቅ አጋጣሚ ነበር። ስለሆነም 'እርሷ እኔን በማግኘቷ አብራቸው ልትሄድ እና ልትሠራ ያለችውን ሴቶች ትታ ከኔ ጋር የምትመለስ ከሆነ ይህቺ ሴት ለኔ ስለማትሆን አላገባትም' ብዬ የእርሷን የኔ መሆን አለመሆኗን ለማረጋገጥ ይህንን እንደ ምልክት አድርጌ ያዝኩ። ይህን ሁሉ ሳስብ የነበረውም እርሷ አግኝታኝ እኔን ሰላም ካለችኝ በኋላ ነበር። ነገር ግን እርሷ ልክ የኔን ሃሳብ የተረዳች ይመስል ከሰላምታዋ በማስከተል በአክብሮት "እርስዎ አሁን ወደ መንደራችን ይሂዱ እና ጸሎት ቤት ውስጥ ሆነው ይጠብቁኝ። እኔም ከባልንጀሮቼ ጋር ሄጄ ሣሩን ሳምጣና እርስዎን ጸሎት ቤት መጥቼ ወደ እኛ ቤት እወስድዎታለሁ።" አለችኝ። ወዲያውም እነርሱ ወደ ሣራቸው ሄዱ። እኔም ወደ ጸሎት ቤቱ አዘግም ጀመር። በዚሁ ጊዜ ልቤ በደስታ ተሞላ። እርሷንም በጣም እንደወደድኳት ይታወቀኝ ጀመር።

ከዚያ በኋላም እኔና እርሷ ለብቻችን ቁጭ ብለን ረዘም ላለ ጊዜ ተወያየን። እኔም መቼ ክርስቶስን እንዳመነች ጠየቅኋት። ስትነግረኝም "ክርስቶስን በማመንሽ ታዲያ ምን ምን ችግር አጋጠመሽ?" ብዬ አልኳት። በዚህ ጊዜ ብዙነሽ ስለ ክርስቶስ የተቀበለችውን መከራ፣ አባቷ ሞተው እርሷን ያሳደጓት የአባቷ እህት (አክስቷ) እንደ ነበሩ፤ እና እኚህ አክስቷ ቃልቻ ስለነበሩ እርሷ ጌታን ባመነችበት ጊዜ "ተይ" ብለው ብዙ መከራ እንዳደረሱባት ነገረችኝ። "አክስቴ ብዙ ጊዜ 'ተይ' ብለው ገርፈውኛል። በዚህ አልመለስ ስላቸውም በገመድ ከምስሶ ጋር አጣብቀው የፊጥኝ በማሰር የቆጮ መቁረጫ ስለታም ቢላዋ አንስተው በእሳት ካጋሉ በኋላ ሲያርዱኝ ወደ እኔ ሲመጡ እኔም ያ ዕለት የመጨረሻዬ እንደሆነ ገብቶኝ "ኢየሱስ ነፍሴን ተቀበል።" እያልኩኝ መጸለይ ጀመርኩ። አክስቴ ይህንን ሲሰሙ ተስፋ ቆርጠው ቢላውን ጣሉ እና ገመዱን ፈትተው ለቀቁኝ።" እኔም ይህንን የእርሷን ምስክርነት ስሰማ ለእርሷ ጥልቅ ፍቅር እና አክብሮት አደረብኝ። ስለ ክርስቶስ መስቀል ፍቅር ዋጋ ከፍላለች ብዬም ደስ አለኝ። በኋላም "ላገባሽ እፈልጋለሁ" ብዬ ነገርኳት። እርሷም ተስማማች።

ከዚያም በጉዳዩ ላይ በብርቱ እንድትጸልይ ነግሬ "ከእኔ ጋር ለወንጌል አገልግሎት በየሃገሩ ትዞሪያለሽ፤ ብዙ ረኃብ፣ ችግር እና መከራ ያጋጥመናል፤ ይህንን ሁሉ አስበሽ እና በደንብ ወስነሽ ጠብቂኝ" አልኳት። እርሷም እኔ እዚያው በነበርኩበት ጊዜ ከእናቷ ምክር ልትጠይቅ ሄደች። ከዚያም ወደ እኔ ተመልሳ መጥታ በሰፊው ተነጋግረን ትዳር ልንመሰርት ተስማማን። በኋላም ትምህርቴን አጠናቅቄ ጌዴኦ ለአገልግሎት ሄጄ ክረምቱን ተመልሼ መጥቼ ቀለል ባለ ሁኔታ በቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ሥርዓት ፈጻሚነት ሠርጋችን ተካሂዶ ትዳር መሰረትን።

ብዙነሽ እስከ ዕለተ ሞቷ ከኔ ጋር ሆና ልታደርገው ቃል ኪዳን የገባችውን ቃሏን ጠብቃ ኖራለች። እኔና እርሷ ለጋብቻ ከተስማማን በኋላ በዚያን ዘመን በአካባቢያችን እንደነበረው ልማድ መተጫጨታችን እንዲታወቅ በጊዜው ምርጥ ቀሚስ ገዝቼ አልብሼያት ነበር ወደ ጌድኦ የዘመትኩት። ሆኖም እርሷ መታጨቷ እየታወቀ አንድ የአካባቢው ባላባት ጠልፎ ሊወስዳት እንዳሰበ መረጃ የደረሳቸው የእርሷ አካባቢ አማኞች ጉዳዩን ለክፍለ ማኅበር መሪ ሽማግሌዎች አሳወቁ። በዚያ ዘመን በኛም ሆነ በአካባቢያችን ባሉ ሕዝቦች ባህል አንድ ሰው የወደዳትን ሴት ጠልፎ ማግባት የሚችል ሲሆን በተለይ ጠላፊው ባላባት ከሆነ ምንም ችግር ስለማያጋጥመው ሁኔታው ከባድ ነበር። የክፍለ ማኅበር መሪዎችም ነገሩን ለከምባታና ሃዲያ አውራጃ መሪዎች ነገረው መሪዎቹ ለአገልግሎት ላሰማሯቸው አገልጋዮች ያላቸውን ፍቅርና አክብሮት በሚያሳይ ሁኔታ በዚያ ዘመን ትልቅ ክብር ከነበራቸው የቤተ ክርስቲያን መሪዎች አንዱ የሆኑት አባ ዶጊሶ ያለሁበት ጌዴኦ ድረስ መጥተው እኔን አገኙኝ። ከዚያም ሁኔታውን ገልጸውልኝ ወደ እኛ አካባቢ ይዘውኝ ተመለሱ።

እኔ ከተመለስኩ በኋላም የሠርጉን ዝግጅት አድርገን እስክንጋባ ድረስ ብዙነሽ እንዳትጠለፍ የኛ ክፍለ ማኅበር መሪዎች "ልጅቱን ከቤተሰቧ ተቀብለን በኛ እጅ እናቆያለን። ከዚያም የቃል ኪዳን ስነ ስርዓቱን እናካሂዳለን›› ብለው ወሰኑ። እኔ ግን ውሳኔአቸውን ሲያሳውቁኝ በጉዳዩ አልተስማማሁም ነበር። ምክንያቱን ሳስረዳም "እኔ ልጅቱን ላገባ ከእርሷ ጋር ብቻ ሳይሆን ከመላ ቤተሰቦቿ ጋርም በፍቅር ለመኖር ነው፤ ስለሆነም ይህ እንዲሆን አልፈልግም። ልጅቱን የሠርግ ስነ ሥርዓት ሳይካሄድ እንዲሁ ወስዳችሁ እናንተ ጋ ብታስቀምጡ ቤተሰቦቿ ያዝናሉ" አልኳቸው።

"ይህ እኔ ተስማምቼ የሚደረግ ከሆነ እኔንም በመልካም ዓይን አያዩኝም። ከዚህ የተነሳም በቀጣይ ዘመን ጥሩ ግንኙነት አይኖረንም። እናንተም ይህንን ነገር ጣልቃ ገብታችሁ ስትፈጽሙ ለመልካም እንዳደረጋችሁት አይቆጥሩም። ስለዚህ እነርሱ ጋብቻችን እንዲፈጸም የሚፈልጉ ከሆነ ከቤታቸው አውጥተው ልጃቸውን ይስጡኝ።" በማለቴ ሽማግሌዎችም ባቀረብኩት ሃሳብ ተስማሙ።

ይህ ሃሳቤ ለልጅቱ ቤተሰብ ሲገለጽላቸውም በጣም ደስ ብሏቸው መረቁኝ። ከዚያም እነርሱም በፍጥነት ልጅቱን ይዘው ለሚወጡ መጠነኛ ቁጥር ላላቸው አጃቢዎች ምግብ እና መጠጥ አዘጋጁ። የሠርጉ ዕለት እኔ በወንጌላዊነት ማገልገል ስለጀመርኩ ለአገልግሎት የምጠቀምበት ኮትና ሱሪዬን በመልበስ አጃቢዎቼን አስከትዬ ሙሽሪት ቤት ሄድኩኝ። የኔ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች የሆኑ ሽማግሌዎችም አጅበውኝ ሄደው ነበር።

ከዚያም ሙሽሪት የገዛሁላትን ቀሚስ ለብሳ በሴቶች ታጅባ ጠበቀችኝ። ቤተሰቦቿም ለአጃቢዎች ያዘጋጁትን ምሳ በልተን ተነስተን ወደ ቤተ ክርስቲያን ሄድን። የሙሽሪት ቤተ ዘመዶችም አጅበውን ቤተ ክርስቲያን ሄደው የሠርጉ ሥነ ሥርዓቱ ዛሬ የጊዮጣ እና የዲኒቃ ክፍለ ማኅበር ተብሎ በተለያየው አጥቢያ (ያኔ አንድ ላይ ነበረ) እዚያ

ጋብቻችን ተፈጸመ። በሠርጉ ሥነ ሥርዓት ላይም አቶ ጉሬቦ የሚባል ሰው ከሰበከ በኋላ የቃል ኪዳን ሥነ ሥርዓቱ የብዙነሽ ቤተ ዘመድ እና የኔ አጃቢዎች በተገኙበት ተካሂዶ ጉዞ ወደ እኔ ቤት ሆነ።

በኔ ቤት በእኔው ውሳኔ በጣም ቀለል ያለ ዝግጅት ያደረግሁ ሲሆን ይህም ያኔ በኛ አካባቢ ይደረግ ከነበረው የሠርግ ድግስ አንጻር አራተኛ ደረጃ የሚሰጠው ዓይነት ነበር።

ይህ እንዲሆን የወሰንኩበት ምክንያት ከኔ ሠርግ አስቀድሞ ገና ወንጌልን ሳናምን በፊት የታላቅ ወንድሜ ሠርግ እኛ ቤት ተደግሶ ነበር። ያ ሠርግ በጣም ትልቅ ሠርግ ከመሆኑ የተነሳ እኛ ሁላችን የለፋነውን ልፋት እና የደከምነውን ድካም ዛሬም ድረስ አስታውሰዋለሁ። በዚያ ሠርግ ላይ 33 ጋን ጠላ የተጠመቀ ሲሆን ብዙ ማር የፈጀ 4 ጋን ጠጅም ተጥሎ ነበር። የምግቡ ዝግጅት ደግሞ መጠን አልነበረውም። በዚህ ጊዜ እኔን በጣም ያሳዘነኝ ያንን ሁሉ ድግስ ደግሰን የአገሩን ሰው ሰብስበን ስናበላ ያ ሁሉ ተሰብስቦ የበላ ህዝብ በልቶ ጠጥቶ ሰክሮ ከጨረሰ በኋላ ወደየ ቤቱ ሲሄድ አብዛኛው ሰው መርቆ ሳይሆን "ወደ እናንተ ቤት ደግሞ ለለቅሶ እንምጣ" እያለ ተራግሞ ነበር የሄደው።

የኔ ሠርግ በደረሰበት ጊዜም ከወንድሜ ሠርግ ትምህርት ወስጄ በፍጹም ትልቅ ሠርግ ላለማድረግ ወስኜ ነበር። ስለሆነም ከሠርጉ በፊት አስቀድሜ ለእናቴ አቋሜን ግልጽ አደረግሁ። በተለይም በወንድሜ ሠርግ የለፋነውን ልፋት የሰጡን ሁኔታ ሁሉ ሳይቀር ርዝሬ ነግሬአቸው አነስተኛ የሠርግ ድግስ ለመደገስ ተስማማን። ከዚያም አንድ ኩንታል ጤፍ እና አንድ እንስራ ማር ብቻ ነበር ያዘጋጀሁት።

ሠርጉ ዕለት የቤተ ክርስቲያን ሥነ ሥርዓት ተጠናቆ ወደ ቤት ከሄድን በኋላ መጠኑ የተዘጋጀውን ምግብ የተጠሩት ዘመዶቼ እና አጃቢዎች እየተመገቡ እያለ እኔ ልጠራቸውም የማያምኑ የአካባቢው ጎረምሶች እና ልጃገረዶች ተሰባስበው እየጨፈሩ መጡ። በዚህ ጊዜ ተነስቼ ወደ ውጪ ወጣሁና ገና ወደ ቤት ሳይጠጉ ወደ እነርሱ ሄጄ አናገርኳቸው። ድሮ እኔም የዚህ ዓይነቱ ጭፈራ ቀንደኛ ተሳታፊ ነበርኩ። "እኔ የድሮ ኬዳሞ አይደለሁም፤ አሁን ሌላ ሰው ነኝ፤ ክርስቶስን በማመኔ ከእናንተ ተለይቻለሁ። በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ እኔ ከአሁን በኋላ በዚህ አገር አልኖርም። ደግሳችሁ ልትጠሩኝ አትችሉም። አሁን እኔ ጋ ስትመጡ ገንዘብ አዋጥታችሁ ትሰጡኛላችሁ። እኔ ግን መልሼ ልከፍላችሁ አልችልም። በዚያ ላይ አሁን እኔ ፈጽሞ ሬንን አልቀበልም። ስለዚህ ከዚሁ ብትመለሱ ይሻላልና ሂዱ።" አልኳቸው። ያኔ ጣቶቹ ለጊዜው ቅር ያላቸው ቢመስሉም ከዚያ በኋላ ግን "ኬዳሞ ነው ቁርጣችንን በጊዜ የነገረን" እያሉ ያመሰግኑኝ ነበር። ከዚያም የጠራኋቸው ሰዎች ብቻ በመጠኑ የተዘጋጀውን ተቃምሰው ብርዝ ጠጥተው ብዙም ሳይቆዩ በጊዜ ተሰናበቱና ሠርጌም ሁ መልኩ ተጠናቀቀ።

ሠርጌ ከተጠናቀቀ በኋላ በመንደሯ ተወዳጅ የነበረችው እና ሰው ሁሉ "ዜና" እያለ ይጠራት የነበረችውን እና እኔ "ብዙነሽ" ያልኳት ሙሽራዬን ይዤ ለአንድ ወር ያህል ብቻ በሻሸ የሙሽርነት ጊዜያችንን እያሳለፍን ቆየን። በኋላም አስቀድሜ እንደነገርኳት እና እንደተስማማችው የወንጌል አገልግሎቴን ለመቀጠል ተያይዘን ወደ ጌዴኦ ተመለስን።

ጌዴኦ ስንደርስም ከሄድኩ ጀምሮ እንደ እናት ተቀብለው ያኖሩኝ ወ/ሮ ለሊዮ በደንብ ተዘጋጅተው ቤት ዘመድ ጠርተው ደግሰው ተቀበሉን። እኔና ባለቤቴንም ዲላ ድረስ መጥቶ የሚቀበለን በቅሎ አዘጋጅተው በክብር ወደ ዲላ ገባን። የጌዴኦ ታሪኬን በተናገርኩበት የመጀመሪያ ክፍል እንደገለጽኩትም ከብዙነሽ ጋር በጌዴኦ የነበረውን ፈተና ሁሉ እየተጋፈጥን አገለገልን። እግዚአብሔርም የመጀመሪያ ልጃችንን ዳዊትን በጌዴኦ እያገለገልን እያለ ሰጠን። ይሁንና ብዙነሽ ከተጋባን ከሁለት ወራት በኋላ የሳምባ በሽታ ይዞአት ያሰቃያት ጀመር። ያም ለቤተባችን ታላቅ ፈተና ሆኖ ለዓመታት እየተቸገርን ኖረናል።